

የንግድ የመንገድ የሕዝብ ትራንስፖርት የኦፕሬተር አደረጃጀት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ እና የስምሪት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 984/2016

Commercial Road Public Transport Operators' Organizational, Competency Assurance Licensing and Trip Implementation Directive No. 984/2024

ጥር 2016 ዓ.ም

January,2024 G.C

መመሪያ ቁጥር 984/2016

የንግድ የመንገድ የሕዝብ ትራንስፖርት የኦፕሬተር አደረጃጀት፣ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ እና የስምሪት አፈፃፀም መመሪያ

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 12(2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የሕዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተር አደረጃጀት፣ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ እና የስምሪት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 984/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "አዋጅ" ማለት የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 ነው፡፡

Directive No. 984/2024

Commercial Road Public Transport Operators' Organizational, Competency Assurance Licensing and Trip Implementation Directive

This Directive is issued by the Ministry of Transport and Logistics in accordance with Article 12 (2) of Road Transport Proclamation No. 1274/2022

Part One

General Provisions

1. Short Title

This Directive may be cited as **"Commercial Road Public Transport Operators' Organizational, Competency Assurance Licensing and Trip Implementation Directive No. 984/2024"**

2. Definitions

In this Directive, unless the context requires otherwise, words shall have the following meanings:

1) "**Proclamation**"means Road Transport Proclamation No. 1274/2022.

2) **"የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ"** ማለት መንገደኞችን እንዲያመላልስ ተብሎ የተሠራ እና ኦፕሬተሩ ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራው በሚኒስቴሩ ዘንድ የሚያስመዘግበው ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፡፡

3) **"የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት"** ማለት ከአንድ የታወቀ መነሻ ወደ ሌላ የታወቀ መድረሻ መንገደኞችንና ቁሳቁሶቻቸውን በታወቀ ክፍያ የማጓጓዝ የትራንስፖርት አገልግሎት ነው፡፡

4) **"የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ"** ማለት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማራ በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልቶ ለተገኘ ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

5) **"ኦፕሬተር"** ማለት አግባብነት ባለው የንግድ ሕግ መሠረት ተመዝግቦ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሰማራት የንግድ ፈቃድ የተሰጠውና በዚህ መመሪያ መሠረት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡

6) **"ደረጃ"** ማለት በዚህ መመሪያ ውስጥ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ለተመዘገበ ኦፕሬተር የሚሰጥ ደረጃ ነው፡፡

2) "**Public Transport Vehicle**": means a motor vehicle designed to carry passengers and the operator registers it with the Ministry for public transport service.

3) "**Public Transport Service**": means a service of transporting passengers and their belongings from one specific departure to another specific destination for a known fee.

4) **"Operator's Competency Assurance License**" means a license issued by the Ministry for operators who wants to engage in the business of public transportation by fulfilling the prescribed criteria under this Directive.

5) **"Operator"** means a person who has a business license from a legally authorized organ to engage in the business of public transportation and registered and licensed as operator in accordance with this Directive.

6) **"Level"** means a level assigned to operator who registered in accordance with this Directive.

7) **“ስቲከር”** ማለት የአፕሬተሩን ደረጃ እና የንግድ ስም የሚገልፅና በተሸከርካሪው አካል ላይ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ የሚለጠፍ መለያ ምልክት ነው፡፡

8) **“ዲስክ”** ማለት የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በዚህ መመሪያ መሠረት ተመዝነው መስፈርቱን ሲያሟሉ ለስምሪት ብቁ መሆናቸውን ማረጋገጫ በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪው የፊት ለፊት ወይም የግንባር መስታወት ላይ እንዲለጠፍ ከሚኒስቴሩ የሚሰጥ ክብ ምልክት ነው፡፡

9) **“ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች“** ማለት አግባብነት ባለው ሕግ የተሰጠው ትርጓሜ እደተጠበቀ ሆኖ የአካል ጉዳተኞችን፣ ነፍሰ ጡር ሴቶችን፣ ሕፃናትን እና አረጋውያንን ያጠቃልላል፡፡

10) **"የተቀናጀ የሕዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተር አስተዳደር ሥርዓት"** ማለት የአፕሬተሩን ዝርዝር መረጃ ማለትም፡- የንግድ ስም፣ የንግድ ምዝገባ ቁጥር፣ የንግድ ፈቃድ ቁጥር፣ አድራሻ፣ የአፕሬተሩን የንግድ አደረጃጀት ዓይነት፣ የኦፕሬተርነት ምዝገባ ቁጥርና ደረጃ፣ የአፕሬተሩን የተሸከርካሪ ዓይነት እና የአሽከርካሪ ማንነትን ዝርዝር መረጃ፣

7) **“Sticker”**means a distinguishing sign that identifies the operator's level and business name and is conspicuously affixed to the body of the vehicle.

8) “**Disc**” means a circular distintingushing mark issued by the Ministry to be affixed on the front or windshield of the public transport vehicle, after fulfilling the criteria set under this Directive as proof that the vehicles are qualified for trip.

9) “**Sections of Society In Need Of Special Support**” means subject to the definition given by the appropriate law; the physically disabled, pregnant women, children and the elderly are included.

10) **“Integrated Public transport operator management system”** means technology system developed by the Ministry to record and control detailed information of operators i.e. business name, business registration number, Business License number, Address, type of organization, operator registration

የኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ስርዓት፣ ለመመዝገብና ለመቆጣጠር የሚያስችል በሚኒስቴሩ የለማ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ነው።

11) **"የኪራይ ውል"** ማለት በኦፕሬተሩ እና የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረት በሆነ ሌላ ሰው መካከል የተፈረመና ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ኪራይ ውል ወይም የትራንስፖርት ስራ ውል ነው።

12) **"የስምሪት መስመር"** ማለት አንድ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ከጉዞ መነሻ እስከ መድረሻ ድረስ ያለውን ርቀት የሚሸፍን የተፈቀደለት የጉዞ መስመር ነው።

13) **"የስምሪት ፕሮግራም"** ማለት የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን የዓመት፣ የወር፣ የሳምንት ወይም የቀን አገልግሎትና እንቅስቃሴን የሚወስን የስምሪት መርሀ-ግብር ነው።

14) **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው።

15) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ነው።

number and level status, details of vehicle and driver and has Electronics payment system.

11) "**Rental Agreement**" means a public transport vehicle rental agreement or Transport work Agreement signed by the operator and the vehicle owner and approved by a body authorized by law to verify and register the agreement.

12) "**Assigned Route**" means the specific departure and destination point to be determined by the Ministry where public commercial road transport vehicles are assigned to operate.

13) "**Trip Schedule**" means yearly, monthly, weekly or daily program scheduled for the operation of public commercial road transport vehicles.

14) **"Minister" or "Ministry"** means the Minister or Ministry of Transport and Logistics, respectively.

15) **"Person"** means any natural or juridical person.

Habtamu Hailemeskel- Legal Consultant & Attorney

16)በአዋጁ አንቀጽ 2 ስር የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደ አግባብነታቸው በዚህ መመሪያም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

17)በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

3. ዓላማ

መመሪያው ተከታዮቹ ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1) ግልጽ የአደረጃጀት ሥርዓት በመዘርጋት በቴክኖሎጂ የታገዘ፣ ጠንካራና ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥና የቁጥጥር ሥርዓትን የሚከተሉ የሕዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተሮችን ማፍራት፤

2) በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችን በማበረታታትና በመደገፍ ተወዳዳሪ ሆነው የሚቀጥሉበትን፣ አዳዲስ ባለሀብቶችም ወደ ዘርፉ የሚገቡበትን ሁኔታ በማመቻቸት የአገልግሎቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ፤

3) የዘርፉ ኦፕሬተሮች አሠራር፣ ብቃትና አደረጃጀት ሀገራችን በሚኖራት አህጉራዊ፣ ቀጠናዊ እና የሁለትዮሽ የመንገድ ትራንስፖርት ትስስር ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ፤

16) Definitions given under Article 2 of the Proclamation shall be applicable to this directive where appropriate.

17) Provisions of this Directive set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

3. Objectives of the Directive

The Directive has the following objectives;

1) To enable the establishment of public transport operators with a transparent and clear system of organization of operators who follow a strong and modern information exchange and control system supported by technological results;

2) To ensure the sustainability of the public transport service by creating enabling situations of the service by facilitating the entry of new investors into the sector.

3) Modernize the operation, efficiency and organization of operators; to make competitive in the regional integration and bilateral transport network.

4) በዘርፉ ከፍተኛ አቅምና ብቃት ያላቸውን ኦፕሬተሮች በፍጠር በመካከላቸው ያለውን ውድድር ከፍ ማድረግና የተቀናጀ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት በመዘርጋት የኅብረተሰቡን የመክፈል አቅም ባገናዘበ መልኩ እንዲንቀሳቀስ ማስቻል

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በሀገር ውስጥ ከአንድ የክልል ከተማ ወደ ሌላ የክልል ከተማ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ለመስጠት፣ እንዲሁም ዓለም-አቀፍ የንግድ የመንገድ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ከሚኒስቴሩ የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በተሰጠው ማንኛውም ኦፕሬተር እና ኦፕሬተሩ በባለቤትነትና በውል በሚያስመዘግባቸው ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4) To increase the competitive and integrated working environment by creating highly capable and competent operators in the sector and to enable the transport of passengers in a cost-effective manner by establishing an integrated public transport service delivery system

4. <u>Scope Of Application</u>

This directive shall be applicable to operator and vehicles the operator make registration as owner and through rental agreement; and who has granted a competency assurance license from the Ministry to engage in public transport services from one regional city to another regional city in the country, as well as to provide international commercial road public transport services.

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>ስለኦፕሬተር የወል ድንጋጌዎች</u>

5. <u>የኦፕሬተር ግዴታዎች</u>

ማንኛውም ኦፕሬተር የሚከተሉት ግዴታዎች አለበት፡፡

Part Two

General Provisions about the Operator

5. <u>Duties of the Operator</u>

Any operator shall have the following duties:

1) በባለቤትነትና በኪራይ ያስመዘገባቸውን ተሽከርካሪዎች፣ በተሽከርካሪዎቹ የተሸፈነ የጉዞ ርቀት፣ የተጓጓዘ ሕዝብ ብዛት፣ የሰው ኃይልና የቢሮ አደረጃጀት፣ ወቅታዊ የሕዝብ ማመላለሻ የጉዞ ዋጋ/ታሪፍ/ መረጃን፣ የአሽከርካሪዎችን፣ የረዳቶችን እና ሌሎች መረጃዎችን አደራጅቶ የመያዝና በወሩ የመጨረሻ ቀናት /ከ25 እስከ 30/ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፤

2) የመንገድ ትራፊክ አደጋን ለመቀነስ የሚያስችል ግልፅ ዕቅድ በማዘጋጀት አተገባበሩንና አፈጻጸሙን የሚመለከት ሪፖርት በየስድስት ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፤

3) በሚኒስቴሩ ወይም በመንገድ ደኅንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት አማካኝነት በሚከናወኑ የመንገድ ደኅንነት ማሻሻያ ተግባሮች ላይ የመሳተፍ፤

4) ሚኒስቴሩ ባዘጋጀው ዝርዝር መስፈርት መሠረት የተዘጋጀና የድርጅቱን ስም፣ አርማ እና የኦፕሬተርነት ደረጃ የያዘ ስቲከር በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ የጋቢና በሮች ውጫዊ አካል ወይም በተሽከርካሪው ግራና ቀኝ ጎኖች ላይ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ የመለጠፍ፤

1) Consolidate data as to the vehicles owned and Rented, the trips covered, volume of passengers transported, personnel and office structure, current market price/tariff/, Details of Drivers, Driver helpers, and any other information; and submit the same to ministry in last five working days of each month/from 25-30/;

2) Prepare a clear plan to reduce road traffic accidents and submit a report to the ministry regarding its implementation and performance every six month;

3) Participate in national road safety activities through the ministry or the Road Safety and Insurance Fund Service.

4) Affix a sticker containing the company name, logo and operator Level on the cab and both sides of the public Transport Vehicle according to the detail criteria prepared by the Ministry;

5) የተሸከርካሪውን የአገልግሎት ምዘና ውጤት እና ደረጃ የሚያሳይ ዲስክ ከሚኒስቴሩ ወስዶ በተሸከርካሪዎች ላይ በግልፅ በሚታይ መልኩ የመለጠፍ፤

6) የዋና መሥሪያ ቤቱን ወይም የቅርንጫፉን አድራሻ ሲቀይር በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ፤

7) በተቀናጀ የሕዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች አስዳደር ሥርዓት ላይ ባስመዘገባቸው የሕዝብ ማመላለሻ ተሸከርካሪዎች ብቻ አገልግሎት የመስጠት እና ተሸከርካሪዎቹ በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጭ በሚሆኑበት ጊዜ ለሚኒስቴሩ በዕለቱ የማሳወቅ፤

8) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በወሰደበት ወቅት ያሟላቸው መስፈርቶች እና የአገልግሎት መመዘኛዎችን ሁል ጊዜ የማክበር እና አሟልቶ የመገኘት፤

9) በተቀናጀ የሕዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች አስዳደር ሥርዓት ያስመዘገቧቸውን ተሸከርካሪዎች እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሥርዓት የመዘርጋትና ለቁጥጥር እንዲያመች በቀን ለ24 ሰዓት እና በሳምንት ለ7 ቀናት የቴክኖሎጂ ሥርዓቱን ለሚኒስቴሩ ክፍትና ተደራሽ የማድረግ፤

5) Affix a Disc on the vehicle which shows the result and Level of Public transport vehicle in visible manner;

6) Notify the Ministry at times of changing the address of the head office or branch within fifteen days;

7) Provide public transportation services only with vehicles registered on the Integrated public Transport Operators Management System; and Notify the ministry on the same day when vehicles are out of service for various reasons;

8) Always comply with and maintain the requirements and service standards that he met at the time of obtaining the qualification certificate;

9) Develop a technology system which helps to follow up and monitor the movement of vehicles and shall make the system open and accessible 24 hours a day and 7 days a week in a way that the Ministry can monitor;

10)በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) የተጠቀሰው የቴክኖሎጂ ሥርዓት ሲበላሽ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጭ ሲሆን በዕለቱ ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ እና ብልሽቱን በዕለቱ በማስተካከል የማሳወቅ፤

11)በኪራይ የያዛቸው የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የኪራይ ውል ሲቋረጥ ውሉ በተቋረጠ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ፤

12)በተለያዩ ምክንያቶች ለአስቸኳይ ሀገራዊ ልዩ ሥራ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪው በሚፈለግበት ጊዜ በሚኒስቴሩ በሚሰጠው የኮታ ድልድል መሠረት የተሰጠውን ተልዕኮ የመፈፀም፤

13)ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም በኪራይ ይዞ ለሚገለገልባቸው የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችና አሽከርካሪዎቻቸው እንደ ባለቤትና አሠሪ ሆኖ ሙሉ ኃላፊነቱን የመውሰድ፤

14)በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች በማሟላት የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በወቅቱ የማሳደስ እንዲሁም ፈቃዱን ቢሮ ውስጥ ለዕይታ በሚያመች መልኩ የማስቀመጥ፤

10) When the technology system mentioned in sub-Article (9) of this Article breaks down or has a malfunction, notify the desk on the same day and to correct the malfunction and notify the desk on the same day;

11) Shall Notify the Ministry within seven working days of the termination of the rent agreement of the public transportation vehicles he has taken on rent;

12) Shall Transport based on the quota allocation given by the Ministry when required by the government for urgent national special transportation service;

13) Shall Take full responsibilities as the owner and employer of the vehicle he has taken on rent and for the implementation of this directive;

14) Shall renew competency assurance license timely by fulfilling the relevant pre-conditions and place on visible manner;

15)በዘርፉ የወጡ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ በሚኒስቴሩ የፀደቁ መመሪያዎችን፣ የአሠራር ሥርዓቶችን እና ማንዋሎችን አክብሮ በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ መሠረት አገልግሎት የመስጠት፤ ግዴታ አለበት፡፡

ክፍል ሦስት
ስለኦፕሬተርነት ፈቃድ

6. የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚያስፈልጉ ሰነዶች

የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም አመልካች፡-

1) የኦፕሬተሩ አድራሻ፡-

ሀ) የሚገለገልበት ቤት የአመልካቹ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ፤

ለ) የሚገለገልበት ቤት የኪራይ ከሆነ የኪራይ ዘመኑ ያላለፈበት እና የኪራይ ውል ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የኪራይ ውል፣

ሐ)ቤቱ የመንግሥት ከሆነ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ውል፤

15) Shall respect proclamation, Regulation, Directives, manuals and procedures enacted by the ministry, and provide services according to the competency assurance license issued.

Part Three

About the Operator's License

6. Documents required for obtaining competency assurance license

Anyone seeking to obtain operator competency assurance license shall complete and submit:

1) Address of the operator:-

A. Proof of ownership if the house is owned by the applicant;

B. If the house to be used is for rent, the rental contract has not expired and has been certified by the document registration and authentication office;

C. If the rental house is government owned, a lease agreement issued by the relevant government agency;

2) በዚህ መመሪያ መሠረት የተቀመጠው የሰው ኃይል የቅጥር ውል፣ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ እና የትምህርት ማስረጃዎች፤

3) የተሸከርካሪው የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብደተር/ሊብሬ/፣ የተሸከርካሪው የቴክኒክ ምርመራ ምስክር ወረቀት፣ የተሸከርካሪው የ3ኛ ወገን መድን ምስክር ወረቀት፣ የንግድ ምዝገባ ፈቃድ ምስክር ወረቀት፣ የፀና የንግድ ፈቃድ ምስክር ወረቀት፣ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ምስክር ወረቀት፣ የአሽከርካሪዎቹ የታደሰ መንጃ ፈቃድ፣ የአሽከርካሪዎቹ የልዩ ሥልጠና ምስክር ወረቀት፣ የአሽከርካሪው፣ የረዳቱ እና የገንዘብ ተቀባዩ መታወቂያና የቅጥር ውል፤

4) ሁሉም ተሽከርካሪዎች ሚኒስቴሩ ባስቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት አገልግሎት የሚሰጥ ጂፒኤስ የተጠመላቸው መሆኑን የሚገልፅ ሕጋዊ ሰነድ፤ እና

5) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተመለከቱትን ሰነዶች ኦሪጂናል መሆናቸውንና ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ በተቀናጀ የሕዝብ ትራንስፖርት አስተዳደር ሥርዓት በመጠቀም አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

2) Employment contract agreement, renewed Identification Card or Passport or Driver's License and Educational credentials set in this Directive;

3) Vehicle ownership title certificate book, vehicle technical inspection certificate, 3rd party insurance of the vehicle, Business Registration License, Business License, Taxpayer Identification Number, Driver's renewed driving license, Special driving perimit Cirtificate and Identification Card and employment contract of drivers, helpers and casher;

4) Legal proof stating that all the vehicles are equipped with a serviceable
GPS according to the standards set by the ministry; and

5) Notwithstanding the provisions of sub-article (1) up to(4) of this Article, complete and submit any other relevant information and documents by verifying their truthfulness through integrated public transport operator management system.

Habtamu Hailemeskel- Legal Consultant & Attorney

7. የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ

1) አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የአክስዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የግል ትራንስፖርት አቋቁመው የንግድ የመንገድ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልጉ የትራንስፖርት ድርጅቶች በዚህ መመሪያ መሠረት ለልዩ ባስ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ወይም ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ሦስት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሚያሟሉት መስፈርት መሠረት ተደራጅተው የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከሚኒስቴሩ ይሰጣቸዋል።
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተደራጅቶ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም አመልካች በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን መረጃዎችና አባሪ ሰነዶች አሟልቶ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት።

7. Operator Competency assurance licensing procedure

1) In accordance with the relevant law, transport companies that want to establish a share company or a private limited company or a private transport and intend to provide commercial road public transport services, according to this directive, cross-border transport services from level one to level three and for domestic transport services at level one and level two Organizations must be organized according to the criteria they meet and obtain an operator's qualification certificate.
2) Any applicant applying for an organized operator qualification license in accordance with sub-article (1) of this article shall submit the application to the Minister together with the information and attached documents mentioned in the directive;

3) ሚኒስቴሩ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ የቀረቡትን ሰነዶች ትክክለኛነት በማረጋገጥና እና በዚህ መመሪያ መሠረት የተቀመጡት መስፈርቶች መሟላታቸውን በመመዘንና አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የኦፕሬተርነት ብቃት ማጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ሚኒስቴሩ የኦፕሬተርነት ብቃት ማጋገጫ ፈቃድ ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገው ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ምክንያት በመጥቀስ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሑፍ መልስ ይሰጣል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና ከአንቀጽ 10 እስከ 22 የተገለፀው በሚኒስቴሩ የሚሰጠው የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በተሽከርካሪዎች ዕድሜ፣ በተሽከርካሪዎች ብዛት እና በተሽከርካሪዎች ወንበር ብዛት መሠረት ይወሰናል፡፡

6) ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተገለፁት የአደረጃጀት ዓይነቶች ውጭ የትራንስፖርት የንግድ ምዝገባ

3) When an application of operator competency license is submitted to it, the Ministry upon verifying the authenticity of the documents and upon ascertaining that requirements set in this directive is fulfilled; and upon the payments of the prescribed service fee, issue Operator competency assurance License.

4) Where the requested Operator competency assurance License cannot be issued according to sub-Article (3) of this article, the Ministry shall notify in writing within five working days the applicant giving reasons therefore.

5) The operator competency licence issued by the Ministry specified in Sub-Article 1 of this Article and Article 10 up to 22 of this Directive is determined based on the age of vehicle, number vehicle and number seat of vehicles.

6) Any person who comes with types of transport business organizations other than described in Sub-Article 1 of this Article shall be treated according

እና ፈቃድ ይዘው ለሚመጡ አመልካቾች በዚህ መመሪያ ለአክስዮን ማኅበር በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣቸዋል፡፡

7) በዚህ መመሪያ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለሚሰጣቸው ኦፕሬተሮች ሚኒስቴሩ የተሽከርካሪ መመዘኛ መስፈርቶችን ያዘጋጃል፡፡

8) የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (6) ድንጋጌ ቢኖርም በሀገራችን ድንበሮች አካባቢ ከሚገኙ የድንበር ከተሞች ወደ ጎረቤት ሀገር የሚሰጥ የአጭር ርቀት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አመልካቹ ከፍ ያለ ደረጃ እንዲሰጠው ካላመለከተ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ በግል ትራንስፖርት መስፈርቶች መሠረት ተደራጅቶ በሚያሟላው የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

8. የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ዓይነቶች

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጡ የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዶች፡-

to the criteria set for Share Company in this Directive and given a competency assurance License.

7) The ministry shall prepare evaluation criteria for licensed operator's vehicles.

8) Despite the provision of sub article (6) of this article, short distance public transport services provided from border cities located near the border of our countries, unless the applicant applies for a higher level, will be granted an operator competency assurance certificate organized according to the requirements of private transport in this directive.

8. Types of Operator Competency Assurance License

Operator Competency Assurance Licenses issued pursuant to this Directive are:

ሀ) ልዩ የሕዝብ ትራንስፖርት የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፣

ለ) ደረጃ 1 የሕዝብ ትራንስፖርት የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፣

ሐ) ደረጃ 2 የሕዝብ ትራንስፖርት የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፣ እና

መ) ደረጃ 3 የሕዝብ ትራንስፖርት የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ናቸው፡፡

A. Special public Transport Operator Competency Assurance License;

B. Level 1 public Transport Operator Competency Assurance License;

C. Level 2 public Transport Operator Competency Assurance License;

D. Level 3 public Transport Operator Competency Assurance License;

9. ልዩ የሕዝብ ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1) በባለቤትነት የሚያስመዘግበው መነሻ የተሸከርካሪ ብዛት 15 መሆን አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ኦፕሬተሩ ከሚያስመዘግባቸው ተሸከርካሪዎች ውስጥ በመጀመሪያው ዓመት 2 ተሸከርካሪዎች ዕድሚያቸው ዜሮ ዓመት መሆን አለበት፤ በተጨማሪም በሁለተኛው ዓመት 3 ተሸከርካሪዎችን፣ በሦስተኛው ዓመት 3 ተሸከርካሪዎችን ዕድሜያቸው ዜሮ ዓመት የሆኑ ተሸከርካሪዎችን ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

9. Special public Transport Share company Operator Competency Assurance License;

1) The initial number of vehicles owned shall be 15;
2) Out of the vehicles that the operator registers under sub article (1) of this article, 2 vehicle in the first year shall be zero years old; In addition 3 vehicle in the second year, 3 vehicles in the third year which are zero years old vehicle shall be registered.

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የተሽከርካሪዎቹ ዕድሜ ከ7 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

4) የተሽከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር 45 ወንበር እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተገለፁትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ከ7 ዓመት ያልበለጠና የወንበር ብዛታቸው ከ45 ወንበር ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ ኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

10. ልዩ የሕዝብ ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1) በባለቤትነት የሚያስመዘግበው መነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 7 መሆን አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ኦፕሬተሩ ከሚያስመዘግባቸው ተሽከርካሪዎች ውስጥ በመጀመሪያው ዓመት 1 ተሽከርካሪዎች ዕድሜያቸው ዜሮ ዓመት መሆን አለበት፤ በተጨማሪም በሁለተኛው ዓመት 1 ተሽከርካሪዎችን፣ በሦስተኛው ዓመት 2 ተሽከርካሪዎችን ዕድሜያቸው ዜሮ ዓመት የሆኑ ተሽከርካሪዎችን ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

3) Subject to the provision of sub article (2) of this article, the age of the vehicles should not exceed 7 years.

4) Vehicle seat number must be 45 seats and above excluding the driver;

5) If the company fulfills the requirements mentioned in the sub-article (1) to (4) of this article, it may hold and use other vehicles whose age is not more than 7 years and their number of seat is not less than 45 with authenticated rental agreement.

10. Special public Transport private Limited company Operator Competency Assurance License

1) The initial number of vehicles owned shall be 7;

2) Out of the vehicles that the operator registers under sub article (1) of this article, 1 vehicle in the first year shall be zero years old; In addition 1 vehicle in the second year, 2 vehicles in the third year which are zero years old vehicle shall be registered.

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የተሸከርካሪዎቹ ዕድሜ ከ7 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

4) የተሸከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር 45 ወንበር እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተገለፁትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ከ7 ዓመት ያልበለጠና የወንበር ብዛታቸው ከ45 ወንበር ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ ኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

11. ልዩ የሕዝብ ትራንስፖርት የግል ትራንስፖርት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1) በባለቤትነት የሚያስመዘግበው መነሻ የተሸከርካሪ ብዛት 5 መሆን አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ኦፕሬተሩ ከሚያስመዘግባቸው ተሽከርካሪዎች ውስጥ በመጀመሪያው ዓመት 1 ተሽከርካሪዎች ዕድሜያቸው ዜሮ ዓመት መሆን አለበት፤ በተጨማሪም በሁለተኛው ዓመት 1 ተሽከርካሪዎችን፣ በሦስተኛው ዓመት 1 ተሽከርካሪዎችን ዕድሜያቸው ዜሮ ዓመት የሆኑ ተሽከርካሪዎችን ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

3) Subject to the provision of sub article (2) of this article, the age of the vehicles should not exceed 7 years.

4) Vehicle seat number must be 45 seats and above excluding the driver;

5) If the company fulfills the requirements mentioned in the sub-article (1) to (4) of this article, it may hold and use other vehicles whose age is not more than 7 years and their number of seat is not less than 45 with authenticated rental agreement.

11. Special public Transport private transport Operator Competency Assurance License

1) The initial number of vehicles owned shall be 5;

2) Out of the vehicles that the operator registers under sub article (1) of this article, 1 vehicle in the first year shall be zero years old; In addition 1 vehicle in the second year, 1 vehicles in the third year which are zero years old vehicle shall be registered.

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የተሸከርካሪዎቹ ዕድሜ ከ7 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

4) የተሸከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር 45 ወንበር እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተገለፁትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ከ7 ዓመት ያልበለጠና የወንበር ብዛታቸው ከ45 ወንበር ያላነሰ ተሸከርካሪዎችን በተረጋገጠ ኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

12. ደረጃ1 የሕዝብ ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1) በባለቤትነት የሚያስመዘግበው መነሻ የተሸከርካሪ ብዛት 30 መሆን አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ኦፕሬተሩ ከሚያስመዘግባቸው ተሸከርካሪዎች ውስጥ በመጀመሪያው ዓመት 2 ተሸከርካሪዎች ዕድሜያቸው ዜሮ ዓመት መሆን አለበት፤ በተጨማሪም በሁለተኛው ዓመት 3 ተሸከርካሪዎችን፣ በሦስተኛው ዓመት 10 ተሸከርካሪዎችን ዕድሜያቸው ዜሮ ዓመት የሆኑ ተሸከርካሪዎችን ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

3) Subject to the provision of sub article (2) of this article, the age of the vehicles should not exceed 7 years.

4) Vehicle seat number must be 45 seats and above excluding the driver;

5) If the company fulfills the requirement mentioned in the sub-article (1) to (4) of this article, it may hold and use other vehicles whose age is not more than 7 years and their number of seat is not less than 45 with authenticated rent agreement.

12. Level 1 Public Transport Share company Operator Competency Assurance License

1) The initial number of vehicles owned shall be 30;

2) Out of the vehicles that the operator registers under sub article (1) of this article, 2 vehicle in the first year shall be zero years old; In addition 3 vehicle in the second year, 10 vehicles in the third year which are zero years old vehicle shall be registered.

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የተሽከርካሪዎቹ ዕድሜ ከ12 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

4) የተሽከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር 45 ወንበር እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተገለፁትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ከ12 ዓመት ያልበለጠና የወንበር ብዛታቸው ከ45 ወንበር ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ ኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

13. ደረጃ1 የሕዝብ ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1) በባለቤትነት የሚያስመዘግበው መነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 15 መሆን አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ኦፕሬተሩ ከሚያስመዘግባቸው ተሽከርካሪዎች ውስጥ በመጀመሪያው ዓመት 2 ተሽከርካሪዎች ዕድሜያቸው ዜሮ ዓመት መሆን አለበት፤ በተጨማሪም በሁለተኛው ዓመት 3 ተሽከርካሪዎችን፣ በሦስተኛው ዓመት 3 ተሽከርካሪዎችን ዕድሜያቸው ዜሮ ዓመት የሆኑ ተሽከርካሪዎችን ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

3) Subject to the provision of sub article (2) of this article, the age of the vehicles should not exceed 12 years.

4) Vehicle seat number must be 45 seats and above excluding the driver;

5) If the company fulfills the requirements mentioned in the sub-article (1) to (4) of this article, it may hold and use other vehicles whose age is not more than 12 years and their number of seat is not less than 45 with authenticated rent agreement.

13. Level 1 Public Transport Private Limited company Operator Competency Assurance License

1) The initial number of vehicles owned shall be 15;

2) Out of the vehicles that the operator registers under sub article (1) of this article, 2 vehicle in the first year shall be zero years old; In addition 3 vehicle in the second year, 3 vehicles in the third year which are zero years old vehicle shall be registered.

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የተሽከርካሪዎቹ ዕድሜ ከ12 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

4) የተሽከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር 45 ወንበር እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተገለፁትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ከ12 ዓመት ያልበለጠና የወንበር ብዛታቸው ከ45 ወንበር ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ ኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

14. ደረጃ 1 የግል ትራንስፖርት የሕዝብ ትራንስፖርት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1) በባለቤትነት የሚያስመዘግበው መነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 5 መሆን አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ኦፕሬተሩ ከሚያስመዘግባቸው ተሽከርካሪዎች ውስጥ በመጀመሪያው ዓመት 1 ተሽከርካሪ ዕድሜው ዜሮ ዓመት መሆን አለበት፤ በተጨማሪም በሁለተኛው ዓመት 1 ተሽከርካሪ፣ በሦስተኛው ዓመት 3 ተሽከርካሪዎች ዕድሜያቸው ዜሮ ዓመት የሆኑ ተሽከርካሪዎችንማስመዝገብ አለባቸው፡፡

3) Subject to the provision of sub article (2) of this article, the age of the vehicles should not exceed 12 years.

4) Vehicle seat number must be 45 seats and above excluding the driver;

5) If the company fulfills the requirements mentioned in the sub-article (1) to (4) of this article, it may hold and use other vehicles whose age is not more than 12 years and their number of seat is not less than 45 with authenticated rent agreement.

14. Level 1 Private Transport Operator Competency Assurance License

1) The initial number of vehicles owned shall be 5;

2) Out of the vehicles that the operator registers under sub article (1) of this article, 1 vehicle in the first year shall be zero years old; In addition 1 vehicle in the second year, 3 vehicles in the third year which are zero years old vehicle shall be registered.

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የተሽከርካሪዎቹ ዕድሜ ከ12 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
4) የተሽከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር 45 ወንበር እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተገለፁትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ከ12 ዓመት ያልበለጠና የወንበር ብዛታቸው ከ45 ወንበር ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን አጥሬተሩ በስሙ ካስመዘገበው ሁለት ዕጥፍ ያህል ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ ኪራይ ውል ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

15. ደረጃ 2 የሕዝብ ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1) በባለቤትነት የሚያስመዘግበው መነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 30 መሆን አለበት፡፡
2) የተሽከርካሪዎቹ ዕድሜ ከ25 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3) የተሽከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር 45 ወንበር እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተገለፁትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ከ25 ዓመት

3) Subject to the provision of sub article (2) of this article, the age of the vehicles should not exceed 12 years.
4) Vehicle seat number must be 45 seats and above excluding the driver;
5) If the company fulfills the requirements mentioned sub-article (1) to (4) of this article, it may hold other vehicle whose age is not more than 12 years and number of seat is not less than 45 up to twice the number of vehicle registered in the name of operator with an authenticated rent agreement.

15. Level 2 Public Transport Share company Operator Competency Assurance License

1) The initial number of vehicles owned shall be 30;
2) The age of the vehicles should not exceed 25 years.
3) Vehicle seat number must be 45 seats and above excluding the driver;
4) If the company fulfills the requirements mentioned in the

ያልበለጠና የወንበር ብዛታቸው ከ45 ወንበር ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ ኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

16. ደረጃ 2 የሕዝብ ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1) በባለቤትነት የሚያስመዘግበው መነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 15 መሆን አለበት፡፡
2) የተሽከርካሪዎቹ ዕድሜ ከ25 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3) የተሽከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር 45 ወንበር እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተገለፁትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ከ25 ዓመት ያልበለጠና የወንበር ብዛታቸው ከ45 ወንበር ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን ኦፕሬተሩ በስሙ ካስመዘገበው ሁለት ዕጥፍ ያህል ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ ኪራይ ውል ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

sub-article (1) to (3) of this article, it may hold and use other vehicles whose age is not more than 25 years and their number of seat is not less than 45 with authenticated rental agreement

16. Level 2 Public Transport Private Limited company Operator Competency Assurance License

1) The initial number of vehicles owned shall be 15;
2) The age of the vehicles should not exceed 25 years.
3) Vehicle seat number must be 45 seats and above excluding the driver;
4) If the company fulfills the requirements mentioned sub-article (1) to (3) of this article, it may hold other vehicle whose age is not more than 25 years and number of seat is not less than 45 up to twice the number of vehicle registered in the name of operator with an authenticated rent agreement.

17. ደረጃ 2 የግል ትራንስፖርት የሕዝብ ትራንስፖርት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1) በባለቤትነት የሚያስመዘግበው መነሻ የተሸከርካሪ ብዛት 5 መሆን አለበት፡፡
2) የተሸከርካሪ ዕድሜ ከ25 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3) የተሸከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር 45 ወንበር እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡
በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተገለፁትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ከ25 ዓመት ያልበለጠና የወንበር ብዛታቸው ከ45 ወንበር ያላነሰ ተሸከርካሪዎችን አፕሬተሩ በስሙ ካስመዘገበው ሁለት ዕጥፍ ያህል ተሸከርካሪዎችን በተረጋገጠ ኪራይ ውል ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

18. ደረጃ 3 የሕዝብ ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1) በባለቤትነት የሚያስመዘግበው መነሻ የተሸከርካሪ ብዛት 30 መሆን አለበት፡፡

17. Level 2 Private Transport Operator Competency Assurance License;

1) The initial number of vehicles owned shall be 5;
2) The age of the vehicles should not exceed 25 years.
3) Vehicle seat number must be 45 seats and above excluding the driver;
4) If the company fulfills the requirements mentioned sub-article (1) to (3) of this article, it may hold other vehicle whose age is not more than 25 years and number of seat is not less than 45 up to twice the number of vehicle registered in the name of operator with an authenticated rental agreement.

18. Level 3 Public Transport Share company Operator Competency Assurance License;

1) The initial number of vehicles owned shall be 30;

2) የተሸከርካሪ ዕድሜ ከ28 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3) የተሸከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር 45 ወንበር እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

4) የአገልግሎት ዘመናቸው ከ25 ዓመት በላይ ሆኗቸው በዚህ ምድብ ውስጥ ፈቃድ የወሰዱ ተሸከርካሪዎች ቢበዛ 3 ዓመት ብቻ የሚቆዩ ሲሆን ይህን ጊዜም አዲስ ተሸከርካሪ ለመተካት እንደ ሽግግር ጊዜ መጠቀም አለባቸው፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (4) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ደረጃውን የሚመጥን ሌሎች አውቶብሶችን ያለገደብ በተረጋገጠ የኪራይ ውል አስመዝግቦ ሊገለገል ይችላል፡፡

19. ደረጃ 3 የሕዝብ ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1) በባለቤትነት የሚያስመዘግበው መነሻ የተሸከርካሪ ብዛት 15 መሆን አለበት፡፡

2) የተሸከርካሪ ዕድሜ ከ28 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

2) The age of the vehicles should not exceed 28 years.

3) Vehicle seat number must be 45 seats and above excluding the driver;

4) Licensed vehicles in this category whose service life is more than 25 years will last for a maximum of 3 years, and this time should be used as a transition period to replace a new vehicle.

5) Subject to the provision of sub article 4 of this article, it may hold and use other vehicles that meet the standards without limitation on a authenticated rent agreement.

19. Level 3 Public Transport private Limited company Operator Competency Assurance License

1) The initial number of vehicles owned shall be 15;

2) The age of the vehicles should not exceed 28 years.

3) የተሸከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር 45 ወንበር እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

4) የአገልግሎት ዘመናቸው ከ25 ዓመት በላይ ሆኗቸው በዚህ ምድብ ውስጥ ፈቃድ የወሰዱ ተሽከርካሪዎች ቢበዛ 3 ዓመት ብቻ የሚቆዩ ሲሆን ይህን ጊዜም አዲስ ተሽከርካሪ ለመተካት እንደ ሽግግር ጊዜ መጠቀም አለባቸው፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (4) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ኦፕሬተሩ በስሙ ካስመዘገባቸው ተሽከርካሪዎች በተጨማሪ ሁለት ዕጥፍ ያህል ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል አስመዝግቦ ሊገለገል ይችላል፡፡

20. ደረጃ 3 የግል ትራንስፖርት የሕዝብ ትራንስፖርት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1) በባለቤትነት የሚይዘው ተሽከርካሪ ብዛት 30 መሆን አለበት፡፡

2) የተሸከርካሪ ዕድሜ ከ28 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3) የተሸከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር 45 ወንበር እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

3) Vehicle seat number must be 45 seats and above excluding the driver;

4) Licensed vehicles in this category whose service life is more than 25 years will last for a maximum of 3 years, and this time should be used as a transition period to replace a new vehicle.

5) Subject to the provision of sub article 4 of this article, it may hold and use other vehicles that meet the standards up to twice the number of vehicle registered in the name of operator with anauthenticated rent agreement.

20. Level 3 Private Transport Operator Competency Assurance License

1) The initial number of vehicles owned shall be 30;

2) The age of the vehicles should not exceed 28 years.

3) Vehicle seat number must be 45 seats and above excluding the driver;

4) የአገልግሎት ዘመናቸው ከ25 ዓመት በላይ ሆኗቸው በዚህ ምድብ ውስጥ ፈቃድ የወሰዱ ተሽከርካሪዎች ቢበዛ 3 ዓመት ብቻ የሚቆዩ ሲሆን ይህን ጊዜም አዲስ ተሽከርካሪ ለመተካት እንደ ሽግግር ጊዜ መጠቀም አለባቸው፡፡

5) በዚህ አደረጃጀት ስር ተሽከርካሪዎችን በኪራይ ውል ይዞ መጠቀም አይቻልም፡፡

21. <u>የአነስተኛ እና መለስተኛ ተሽከርካሪዎች አክሲዮን ማኅበር ምድብ ለድንበር ተሻጋሪ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1) በባለቤትነት የሚያስመዘግበው መነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 50 መሆን አለበት፡፡

2) የተሽከርካሪ ዕድሜ ከ10 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3) የተሽከርካሪ የወንበር ብዛት አሽከርካሪውን ሳይጨምር ከ8 እስከ 44 ወንበር መሆን አለበት፡፡

4) ይህ አደረጃጀት በልዩ ሁኔታ ለአክሲዮን ማኅበር ብቻ የተፈቀደ ነው፡፡

4) Licensed vehicles in this category whose service life is more than 25 years will last for a maximum of 3 years, and this time should be used as a transition period to replace a new vehicle.

5) Under this organization,it shall not be allowed to hold and use vehicles with rental agreement.

21. <u>Small and Medium Vehicles Share company Category for Cross-Border Operator competency Assurance Licence</u>

1) The initial number of vehicles owned shall be 50;

2) The age of the vehicles should not exceed 10 years.

3) Vehicle seat number must be between 8 and 44 seats excluding the driver.

6) This this category shall be allowed only for share companies under special circumstances.

22. በኪራይ ስለሚመዘገብ ተሽከርካሪ

1) ማንኛውም ኦፕሬተር በስሙ ካስመዘገባቸው ተሽከርካሪዎች በተጨማሪ ተሽከርካሪዎችን በኪራይ ውል ሲይዝ የተሽከርካሪ የኪራይ ውል የቆይታ ጊዜ ቢያንስ ለአንድ ዓመት መሆን አለበት፡፡
2) ማንኛውም ተሽከርካሪን በኪራይ የያዘ ኦፕሬተር የተከራየውን ተሽከርካሪ አስመርምሮ በተመዘገበበት ደረጃ ለአገልግሎት ብቁ መሆኑን የሚያረጋግጥ ዲስክ መውሰድና በተሽከርካሪው ላይ መለጠፍ አለበት፡፡
3) ማንኛውም ተሽከርካሪን በኪራይ የያዘ ኦፕሬተር በተከራየው ተሽከርካሪ አካል ላይ በዚህ መመሪያ ውስጥ ከተጠቀሰው ከራሱ መደበኛ ስቲከር በተጨማሪ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ ልዩ ስቲከር እንዲለጠፍ ማድረግ አለበት፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በኪራይ ተሽከርካሪ ላይ የሚለጠፈው ልዩ ስቲከር ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው መስፈርት መሠረት ይሆናል፡፡

22. About The Vehicle Registered For Rent

1) Any operator in addition to its own registered vehicle owns a vehicle by rental agreement; the rental agreement period of a vehicle is shall be at least for one year.
2) Any operator of a rental vehicle must inspect the rental vehicle and take a disc confirming that it is fit for service to the required level and put it into operation;
3) Any operator who owns a vehicle for hire shall affix special sticker of the company according to the criteria to be set by the ministry in a clearly visible manner on the body of the vehicle for hire as specified in this Directive.
4) The sticker mention under sub Article (3) of this Article shall be determined by the criteria prepared by the ministry.

23. <u>የሕዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተር የአገልግሎት ወሰን</u>

1) በልዩ ባስ ትራንስፖርት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ ኦፕሬተር በሀገር ውስጥ እና በዓለም ዓቀፍ የመንገድ የሕዝብ ማመላሻ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡
2) ማንኛውም በሀገር ውስጥ እና በዓለም ዓቀፍ የመንገድ የሕዝብ ማመላሻ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ኦፕሬተር በሀገር ውስጥ ዋና ጽ/ቤት የሚኖረው ሲሆን በመዳረሻ ሀገር አንድ ወኪል ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊኖረው ይገባል፡፡
3) ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በዓለም ዓቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በሀገራቱ የሁለትዮሽ ስምምነት መሠረት ለተሸከርካሪው የተዘጋጀውን የድንበር መሻገሪያ ፈቃድ፣ ለአሽከርካሪ እና ለረዳት የድንበር መሻገሪያ መታወቂያ መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡
4) ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ ኦፕሬተር በሀገር ውስጥ የመንገድ የሕዘብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ብቻ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

23. <u>Scope Of Service of Public Transport Operators</u>

1) Operators who have received special bus certificate of competence assurance of public transport shall provide domestic and international road public transport services.
2) Any operator who provides domestic and international road public transport services shall have one head office in the country and one agent or branch office in the country of destination.
3) Subject to the provision of sub article (1) and (2) of this article, to provide international road transport service; they shall receive cross-border permit for vehicle, Driver and Driver helper based on the countries bilateral agreement.
4) Operator that has received level 1 or level 2 or level 3 competency Assurance license shall provide domestic road freight transport services.

5) የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ወሰን በተሽከርካሪ የአካባቢ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ልዩነት የማይደረግበት ሲሆን በክልሎች መካከል የሚኖረውን የትራንስፖርት ትስስር መተመለከተ በሚያቀርቡት መርሀ-ግብር መሠረት ይሆናል፡፡

24. የአነስተኛና መለስተኛ የሕዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የአገልግሎት ወሰን

1) በክልሎች ወይም በከተማ አስተዳደሮች እና በፌደራል መናኸሪያዎች የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ አነስተኛና መለስተኛ በደረጃ 1፣ በደረጃ 2 እና በደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰዱ ኦፕሬተሮች በክልሉ ውስጥ እና በኩታ-ገጠም ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮችን በሚያገናኙ መንገዶች ላይ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡
2) በክልሎች፣ በከተማ አስተዳደሮች እና በፌደራል መናኸሪያዎች የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ አነስተኛና መለስተኛ በደረጃ 1፣ በደረጃ 2 እና በደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰዱ ኦፕሬተሮች በፀደቀላቸው የጉዞ ፕሮግራም ወይም መርሀ-ግብር በክልሉ ውስጥ እና በኩታ-ገጠም ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን በሚያገናኙ መንገዶች ላይ አገልግሎት የሚሰጡ ሆኖ፡-

5) The scope of service of public transport service shall not be limited by the difference on the area code of vehicle plate idenetifacation number; and the transport integration between regions shall be based on the trip schedule they present.

24. Scope Of Service for small and medium Public Transport Operators

1) Small and medium-sized public transport service providers in the regions, city administrations and federal centers, who have received a certificate of qualification at level 1, level 2 and level 3, will provide services in the region and in Area on the roads connecting the regions and city administrations.
2) Small and medium-sized public transport service providers in the regions, city administrations and federal districts who have received a certificate of qualification at level 1, level 2 and level 3 shall operate based on the trip schedule and:

ሀ) አነስተኛ የወንበር ብዛት ከ8-20 ያላቸው ተሽከርካሪዎች ከመነሻ መናኸሪያ እስከ 200 ኪሎ ሜትር የርቀት ወሰን ድረስ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡፡

ለ) መለስተኛ የወንበር ብዛት ከ21-44 ያላቸው ተሽከርካሪዎች ከመነሻ መናኸሪያ እስከ 300 ኪሎ ሜትር የርቀት ወሰን ድረስ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡፡

ሐ) ከላይ በተቀመጠው የተሽከርካሪዎቹ የጉዞ ርቀት መሠረት የጉዞ ስምሪት በማድረግ ከመናኸሪያ ተነሺ የሆነ ተሽከርካሪ ወደ ጉዞ መድረሻ ጣቢያ /መናኸሪያ/ ሲጓዝ የተፈቀደለት የጉዞ ርቀት ከመድረሻው ቦታ ሳይደርስ የሚያበቃ ከሆነ በ20 ኪሎ ሜትር ውስጥ ወዳለው ቀጣይ መናኸሪያ መንገደኞቹን ማድረስ አለበት፡፡

3) በኦፕሬተሮች መካከል የሚደረግ ማንኛውም ውድድር የትራንስፖርት ሕግና ደንብን በጠበቀ አግባብ መፈፀም የሚኖርበት ሆኖ ውድድሩም በአገልግሎት ጥራት፣ በዋጋ እና በሌሎች ተሳፋሪውን በሚስቡ ተግባራት የታገዘ እንዲሆንና በተመሳሳይ ኪሎ ሜትር በሚሸፈኑ መስመሮች ላይ ከፍተኛ የወንበር ብዛት ያላቸው ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡

a) Vehicles with a minimum number of seats of 8-20 can provide service up to a distance of 200 kilometers from the point of origin.

b) Vehicles with the minimum number of seats from 21-44 can serve up to a distance of 300 kilometers from the starting point;

c) According to the travel distance of the vehicles set above, when a vehicle departing from terminal travels to the destination station /terminal/, if the allowed travel distance ends before reaching the destination, the vehicle shall take the passengers within 20 kilometers to the next station.

3) Any competition between operators should be conducted in accordance with the transport laws and regulations, and the competition should be based on the quality of service, price, and activities that attract the passengers and on routes that cover the same kilometer, vehicles with the highest number of seat shall get priority.

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2) ፊደል /ሀ/ እና /ለ/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኦፕሬተሮች በአንድ ክልል የፀደቀ የስምሪት መርሀ-ግበር በሌላኛው ኩታ-ገጠም ክልል እና በፌደራል መናኸሪያ ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡

5) በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች በጋራ በሚሸፈኑ የኩታ-ገጠም የስምሪት መስመሮች ላይ ባላቸው የርቀት ወሰን መሠረት የጉዞ ታሪፍ ተመሳሳይና ወጥ መሆን አለበት፡፡

6) የተሽከርካሪዎች የወንበር ብዛት በሚወጣው የተሽከርካሪ መስፈርት መሠረት ከክልል ክልል ያለ ልዩነት ወጥ መሆን አለበት፡፡

7) በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱትና በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር አማካኝነት የሚደራጁ ኦፕሬተሮች የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡት በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ የክልል ወይም ከተሞች መካከል ሲሆን ከሚኒስቴሩ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ መውሰድ አለባቸው፡፡

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ኦፕሬተሮቹ በአንድ ክልል ውስጥ ባሉ ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ ከተሞች መካከል የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ አግባብነት ካለው

4) Subject to the provisions of sub-article (1) (a) and (b) of this article, the trip schedule approved for operators in one region will be implemented at the federal terminal in the other Bordering area region;

5) Tariff will be uniform across states and city administrations on the basis of their distance limits on the shared/combined routes.

6) The number of seat of vehicles shall be uniform according to the vehicle specification issued without any difference from region to region.

7) If the operators mentioned in this article and organized through regional or city administrations provide public transport services between cities in two or more regions, and shall have operator competency assurance licence from the Minister;

8) Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this article, since the operators provide public transport services between cities in the same region, they shall have operator

የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር አካል የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ መውሰድ አለባቸው፡፡

25. <u>የሰው ኃይል አደረጃጀት፣ ተፈላጊ ችሎታ እና የሥራ ልምድ</u>

1) በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በአክሲዮን ማኅበር ወይም በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፣ ወይም በግል ትራንስፖርት ኦፕሬተር ማሟላት ያለበት ዝቅተኛ የሰው ኃይል አደረጃጀት፣ ተፈላጊ ችሎታ እና የሥራ ልምድ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንረዥ "ሀ" እና "ለ" መሠረት ይሆናል፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም 5 ተሽከርካሪዎችን ብቻ ይዞ በግል ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ኦፕሬተር ቢያንስ 1 ሥራ አስኪያጅ እና 1 የሒሳብ ባለሙያ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ለ" የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ፣ የትምህርት ዓይነት እና የሥራ ልምድ እንዲያሟላ አይገደድም፡፡
3) ሚኒስቴሩ በማንኛውም ጊዜ በሚያደርገው ክትትልና ቁጥጥር የአንድ ድርጅት የሰው ኃይል አደረጃጀት የኦፕሬተርነት ብቃት

competency assurance licence from the appropriate regional or city administration.

25. <u>Structure of Human Resources, Qualification and Work Experience</u>

1) The minimum structure of human resource, qualification and work experience required for an operator who wants to engage in public transport share company or Private limited company or private transport shall be according to the table "A" and "B" attached to this directive.
2) Notwithstanding sub article (1) of this article An operator who wants to engage in private transport services with less than 5 trucks shall have at least 1 manager and 1 accountant but the required level of education, qualification and work experience set under table B of this directive is not mandatory.
3) If the Ministry, through its monitoring and control at any time, confirms that the human resource structure of an organization is at a level that

ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠበትን አገልግሎት ለመስጠት በማያስችለው ደረጃ ላይ መሆኑን ካረጋገጠ ለድርጅቱ የተሰጠውን ደረጃ ሊቀንስ፣ ወይም ለድርጅቱ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል።

4) ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3) የተመለከተውን አስተዳደራዊ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ለድርጅቱ የሰው ኃይል አደረጃጀቱን እንዲያስተካክል ከአንድ ወር ያልበለጠ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

26. ስለ ኦፕሬተሩ የንግድ ሥራ መለያዎች

ማንኛውም ኦፕሬተር፡-

1) አድራሻው በግልፅ የሚታወቅ ቢሮ ሊኖረው ይገባል፡፡
2) ክብ ማኅተም ሊኖረው ይገባል፡፡
3) የድርጅቱን ስም፣ ዓርማ አድራሻ የያዘ ስቲከር ማሳተምና በዚህ መመሪያ መሠረት በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪው ላይ መለጠፍ አለበት፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰውና ማንኛውም ኦፕሬተር ለደረጃው የተቀመጠውን ቀለም የያዘ ስቲከር የመለጠፍ ግዴታ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የስቲከሩ

does not allow it to provide the services for which the operator's license has been granted, it may reduce the level given to the company or cancel the competency assurance license given to the organization.

4) Before taking the measures referred to in sub-Article (3) of this article, the minister shall give a one-month warning to the company to adjust its personnel structure

26. About the operator's business accounts

Any operator:

1) Shall have office with and officially known address;
2) Shall have a circular seal;
3) Shall imprint a sticker containing the company's name, logo and address and posted on the cab of the truck;
4) All types of operators referred to in sub-Article (3) of this article should post a sticker with the color set for the level, and the color of category of the sticker and the text will be as follows:

መደብ እና የጽሑፉ ቀለም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ) ለልዩ የሕዝብ ትራንስፖርት (በአክሲዮን ማኅበር፣ በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም በግል ትራንስፖርት) የሚሰጥ ስቲከር የስቲከሩ ቅርፅና መጠን፡-

1) ሙሉ ክብ ሆኖ 40 ሣ.ሜ በ40 ሣ.ሜ የሆነ፤
2) የስቲከሩ የመደብ ቀለም፡-ነጭ፤
3) የጽሑፉ ቀለም፡-ጥቁር፤
4) የጽሑፉ ቋንቋ አማርኛ እና እንግሊዝኛ ሆኖ የድርጅቱን አድራሻ የሚገልፅና በተጨማሪም በስቲከሩ ግራ እና ቀኝ የሚኒቴሩን ሎጎ የያዘ መሆን አለበት፡፡

ለ) ለደረጃ 1 የሕዝብ ትራንስፖርት (በአክሲዮን ማኅበር፣ በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም በግል ትራንስፖርት) የሚሰጥ ስቲከር የስቲከሩ ቅርፅና መጠን፡-

1) ሙሉ ክብ ሆኖ 40 ሣ.ሜ በ40 ሣ.ሜ የሆነ፤
2) የስቲከሩ የመደብ ቀለም፡-አረንጓዴ፤
3) የጽሑፉ ቀለም፡-ነጭ፤
4) የጽሑፉ ቋንቋ አማርኛ እና እንግሊዝኛ ሆኖ የድርጅቱን አድራሻ የሚገልፅና በተጨማሪም የሚኒቴሩን ሎጎ በስቲከሩ ግራ እና ቀኝ ያለው መሆን አለበት፡፡

a) For Special public transport (for share company or private limited company or private transport) The shape and size of the sticker is:
   1) 40 cm by 40 cm in full circle,
   2) The color of the sticker background is: White;
   3) The color of the text is: Black;
   4) The language of the text is Amharic and English, which describes the company's address and also the Ministry of Transport and Logistics logo should be on the left and right.

b) For Level 1 public transport (for share company or private limited company or private transport) The shape and size of the sticker is:

   1) 40 cm by 40 cm in full circle;
   2) The color of the sticker background is: Green;
   3) The color of the text is: White;
   4) The language of the text is: Amharic and English, which describes the company's address and also the Ministry of Transport and Logistics logo, should be on the left and right.

ሐ) ለደረጃ 2 የሕዝብ ትራንስፖርት (በአክሲዮን ማኅበር፣ በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም በግል ትራንስፖርት) የሚሰጥ ስቲከር የስቲከሩ ቅርፅና መጠን፡-

1) ሙሉ ክብ ሆኖ 40 ሣ.ሜ በ40 ሣ.ሜ የሆነ፤
2) የስቲከሩ የመደብ ቀለም፡-ሰማያዊ፤
3) የጽሑፉ ቀለም፡-ነጭ፤
4) የጽሑፉ ቋንቋ አማርኛ እና እንግሊዝኛ ሆኖ የድርጅቱን አድራሻ የሚገልፅና በተጨማሪም የሚኒቴሩን ሎጎ በስቲከሩ ግራ እና ቀኝ ያለው መሆን አለበት፡፡

መ) ለደረጃ 3 የሕዝብ ትራንስፖርት (በአክሲዮን ማኅበር፣ በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም በግል ትራንስፖርት) የሚሰጥ ስቲከር የስቲከሩ ቅርፅና መጠን፡-

1) ሙሉ ክብ ሆኖ 40 ሣ.ሜ በ40 ሣ.ሜ የሆነ፤
2) የስቲከሩ የመደብ ቀለም፡-ቢጫ፤
3) የጽሑፉ ቀለም፡-ጥቁር፤
4) የጽሑፉ ቋንቋ አማርኛ እና እንግሊዝኛ ሆኖ የድርጅቱን አድራሻ የሚገልፅና በተጨማሪም በስቲከሩ ግራ እና ቀኝ የሚኒቴሩን ሎጎ የያዘ መሆን አለበት፡፡

C) For Level 2 public transport (for share company or private limited company or private transport) The shape and size of the sticker is:

1) 40 cm by 40 cm in full circle;
2) The color of the sticker background is: Blue;
3) The color of the text is: White;
4) The language of the text is: Amharic and English, which describes the company's address and also the Ministry of Transport and Logistics logo should be on the left and right.

d) For Level 3 public transport (for share company or private limited company or private transport) The shape and size of the sticker is:

1) 40 cm by 40 cm in full circle;
2) The color of the sticker background is: Yellow;
3) The color of the text is: Black;
4) The language of the text is - Amharic and English, which describes the company's address and also the Ministry of Transport and Logistics logo should be on the left and right.

ሠ) በኪራይ ውል ለሚመዘገብ የሕዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪ (በአክሲዮን ማኅበር፣ በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም በግል ትራንስፖርት) የሚሰጥ ስቲከር የስቲከሩ ቅርፅና መጠን፡-

1) ሙሉ ክብ ሆኖ 40 ሣ.ሜ በ40 ሣ.ሜ የሆነ፤
2) የስቲከሩ የመደብ ቀለም፡-ቀይ፤
3) የጽሑፉ ቀለም፡-ነጭ፤
4) የጽሑፉ ቋንቋ አማርኛ እና እንግሊዝኛ ሆኖ የአከራዩን አድራሻ የሚገልፅና በተጨማሪም በስቲከሩ ግራ እና ቀኝ የሚኒቴሩን ሎጎ የያዘ መሆን አለበት፡፡

e) For vehicle register for Rent (for share company or private limited company or private transport) the shape and size of the sticker is:

1) All side 40 c.m in full circle;
2) The color of the sticker background is: Red;
3) The color of the text is: White;
4) The language of the text is : Amharic and English, with the address of the rental company.

27. <u>የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ዕድሳት</u>

መስፈርቱን አሟልቶ ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ ማንኛውም ኦፕሬተር፡-

1) በየዓመቱ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈፀም የኦፕሬተር ማረጋገጫ ፈቃዱን ማሳደስ፤ እና
2) የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የተቀመጡትን መስፈርቶች በዕድሳት ወቅትም አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡

27. <u>Renewal Of Operator's competency assurance Certificate</u>

Any operator who meets the requirements and obtains an operator's competency Assurance license from the Ministry:

1) Shall renew its operator's competency Assurance license by paying the required service fee every year; and
2) Shall fulfill the criteria set to obtain the operator competency assurance license during renewal period.

28. የደረጃ ማሻሻያ እና ክለሳ

1) በዚህ መመሪያ መሠረት ደረጃ የተሰጠው ኦፕሬተር ለተመዘገበበት ደረጃ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ካሻሻለ ወይም ካጓደለ ሚኒስቴሩ የኦፕሬተሩን ደረጃ በዚሁ ለውጥ መሠረት ሊያሳድግ ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

2) በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 10 እስከ 22 ድንጋጌዎች በተመለከቱት መስፈርቶች ለአደረጃጀት ዓይነትና ደረጃ የተቀመጠውን የመነሻ ተሽከርካሪ ብዛት በተቀመጠው ጊዜ ገደብ መሠረት ኦፕሬተሩ አሟልቶ ካልተገኘ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

29. የሕዝብ ትራንስፖርት ማመላለሻ የጉዞ ዋጋ/ታሪፍ/

1) በደረጃ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ኦፕሬተሮች ሚኒስቴሩ በሚያወጣላቸው ሕጋዊ ታሪፍ የሚሠሩ ሲሆን ግልፅ በሆነ የውድድር ሥርዓት ላይ የተመሠረተ አገልግሎት ተደራሽ እንዲያደርጉ በመካከላቸው የአገልግሎት ታሪፍ ልዩነት ይኖራቸዋል፡፡

28. Level Amendment and Revision

1) If the operator rated with a given level according to this directive improves or fails to comply with the listed requirements, the Ministry may upgrade or lower the operator's level.

2) If the operator does not meet the number of initial vehicles set for the type and level of organization according to the criteria indicated under from Article 10 to 22 within the time limit, the operator competency Assurance license shall be canceled

29. Public transport service fee/tariff/

1) Operators that provide standard public transport services will work with the legal tariff issued by the Ministry and will have service tariff differences between them in order to provide access to services based on a clear competitive system.

2) በደረጃ 1 እና በደረጃ 2 ኦፕሬተሮች መካከል የ30% የአገልግሎት ታሪፍ ልዩነት ይኖራል፤ ይህም ማለት የደረጃ ሁለት ታሪፍ ከደረጃ አንድ በ30% ዝቅ የሚል ሆኖ ይወጣል ማለት ነው፡፡

3) በደረጃ 2 እና በደረጃ 3 ኦፕሬተሮች መካከል 20% የአገልግሎት ታሪፍ ልዩነት ይኖራል፤ ይህም ማለት የደረጃ ሦስት ታሪፍ ከደረጃ ሁለት በ20% ዝቅ የሚል ሆኖ ይወጣል ማለት ነው፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) በተመለከተው አግባብ የጉዞ ዋጋ/ታሪፍ/ ሲዘጋጅ የደረጃ 1 ኦፕሬተር ታሪፍ ከደረጃ 2 ኦፕሬተር በ30% ከደረጃ 3 ደግሞ በ50% ብልጫ እንዲኖረው ተደርጎ ይፀድቃል፡፡

5) ለልዩ ሀገራዊ ተልዕኮ ወይም ግዳጅ ሥራ የተሸከርካሪ ስምሪት የሚፈልግ ማንኛውም አካል በሚኒስቴሩ አመቻችነት ከኦፕሬተሮች ጋር የአገልግሎት ክፍያን፣ የንብረት ጉዳት ማካካሻን እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚያካትት ሕጋዊ የውል ስምምነት በመፈፀም ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2) There will be a 30 percent (30%) service tariff difference between Level 1and Level 2 operators meaning Level 2 fares will be 30% lower than Level 1).

3) There will be a 20 percent (20%) service tariff difference between Level 2 and Level 3 operators (meaning Level 3 fares will be set 20% lower than Level 2).

4) Tariff set under sub article 2 and 3 of this article, when the service tariff is prepared; the fare of level 1 operator is approved to be 30% higher than level 2 and 50% higher than level 3.

5) Anybody that wants to deploy a vehicle for a special national mission (mandatory work) should implement a legal contract with the transporters that includes service fees, property damage compensation and other issues with the facilitation of the Ministry.

ክፍል አራት

የሕዝብ ትራንስፖርት ስምሪት አፈጻጸም እና ቁጥጥር ሥርዓት

30. የሕዝብ ትራንስፖርት ስምሪት አፈጻጸም

ማንኛውም ኦፕሬተር ወይም ስምሪት የተሰጠው ተሽከርካሪ፡-

1) ተሽከርካሪውን በሚመለከተው አካል በተዘጋጀለት ሕጋዊ መናኸሪያ ውስጥ በማስገባት ወይም የልዩ ባስ ከሆነ በራሱ ወይም ከሌሎች ጋር በጋራ በመሆን ባዘጋጀው ደረጃውን የጠበቀ እና ሕጋዊ ዕውቅና ከተሰጠው የተሽከርካሪ መቆሚያ ስፍራ ብቻ ተጓጉዞችን መጫን አለበት፡፡
2) ሕዝብን በሚያጓጉዝበት ጊዜ አግባብነት ካለው መናኸሪያ የተሰጠ መውጫ በመያዝ መሰማራት አለበት፡፡
3) በልዩ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ኦፕሬተር አገልግሎቱን መስጠት የሚጀምረው በየቀኑ ከሌሊቱ 9፡30 ጀምሮ ሲሆን ሁሉም ተጓጉዞች ከተገኙ ከሌሊቱ ከ10፡00 ጀምሮ ወደ ስምሪት መስመሩ መውጣት ይችላል፤ ሆኖም ግን ሁሉም ተሳፋሪዎች ተሟልተው ካልተገኙ እስከ ሌሊት 10፡30 ድረስ ቀሪ ተጓጉዞችን የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

Part Four

Public Transport Trip Implementation and Control System

30. Public Transport Trip Implementation

Any operator or vehicle granted trip:

1) shall enter the vehicle in a terminal prepared by the relevant body or, in the case of a special bus, must board the passenger from a standardized and legally recognized vehicle stop or terminal prepared by him or jointly with others.
2) Shall have a designated exit from the relevant terminal/ station while transporting the public by vehicle.
3) Operators who provide special public transport services start their service from 3:30 p.m. every day, and if all passengers are available, they can go out to the distribution line from 4:00 p.m.; however, if all the passengers are not present, it is mandatory to wait for the remaining passengers until 4:30 pm.

4) በደረጃ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ኦፕሬተር አገልግሎቱን መስጠት የሚጀምረው ከሌሊቱ 11፡00 ጀምሮ ሲሆን ሁሉም ተጓገዞች ከተገኙ ከሌሊቱ 11፡30 ጀምሮ በተፈቀደለት የስምሪት መስመር መውጣት ይችላል፤ ሆኖም ግን ሁሉም ጓገዞች ተሟልተው ካልተገኙ እስከ ሌሊቱ 12፡00 ድረስ ቀሪ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

5) ከየትኛውም መናኸሪያ ለሕዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪ ስምሪት መስጠት የሚቻለው ከመነሻው እስከ መድረሻ ያለው የጉዞ ርቀት፡-

ሀ) 300 ኪ.ሜ እና ከዚያ በላይ ከሆነ እስከ ቀኑ 6፡00 ሰዓት ድረስ፤

ለ) ከ300 ኪሎ ሜትር በታች ሆኖ ከ200 ኪ.ሜ በላይ ከሆነ እስከ ቀኑ 8፡00 ሰዓት ድረስ፤

ሐ) ከ200 ኪ.ሜ በታች 100 ኪ.ሜ በላይ ከሆነ እስከ ቀኑ 11፡00 ሰዓት ድረስ፤

መ) 100 ኪ.ሜ እና ከዚያ በታች ከሆነ እስከ ምሽቱ 2፡00 ሰዓት ድረስ፤

6) ለተጓገዞች አገልግሎት ሲሰጥ መነሻው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (5) የተደነገገው ቢኖርም መድረሻው ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት ማለፍ የለበትም፡፡

4) An operator providing regular public transport services will start providing the service from 5:00 p.m. and if all passengers are available, they can leave from 5:30 p.m. through the approved route; however, if all passengers are not available, they will be required to wait until 6:00 midnight.

5) The trip schedule provide for public transportation vehicles the travling distance from origion to destination shall be:

a) until 12:00 p.m. if the travel distance is 300 k.m and more;

b) until 2:00 p.m. if the travel distance is less than 300 km and above 200 k.m;

c) until 5:00 p.m. if the travel distance is less than 200 k.m and above 100 k.m.;

d) Until 8:00 p.m. if the travel distance is 100 km and less.

6) Any operator providing public transport services shall not exceed 9:00 p.m. at the time of departure, subject to the provisions of sub-paragraphs /5/ of this article.

7) ከመነሻው መናኸሪያ መውጫ ፈቃድ የወሰደ የሕዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪ በክልል ከተሞች በሚገኙ ማናቸውም መናኸሪያዎች ገብቶ እስከ 45 ደቂቃ ያህል የመቆየት፤ በዞን ከተሞች በሚገኙ መናኸሪያዎች ደግሞ እስከ 30 ደቂቃ ያህል መቆየት ይችላል፡፡

8) በተሽከርካሪው የወንበር ብዛት መጫን እና ለመስመሩ በተፈቀደው የጉዞ /ታሪፍ/ መሠረት አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

9) እስከ 25 ኪሎ ግራም ድረስ ለሚመዝን የተጓዥ ቁሳቁስ ያለተጨማሪ ክፍያ ማጓጓዝ ያለበት ሆኖ ጭነቱን ለመጫን እና ለማውረድ የሚከፈለው አገልግሎት ክፍያ በኦፕሬተሩ ይሸፈናል፡፡

10) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከ25 ኪሎ ግራም በላይ ለሚመዝን የተጓዥ ቁሳቁስ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው የታሪፍ ልክ ብቻ ማስከፈል አለበት፡፡

11) ተሽከርካሪዎቹን ለስምሪት ዝግጁ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ሚዛን፣ የደንብ ልብስ፣ ባጅ እና የመሳሰሉትን አዘጋጅቶና አሟልቶ የማቅረብ እንዲሁም በመናኸሪያ አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞቹ ተገቢውን የደንብ ልብስ እና ባጅ እንዲያደርጉ ማድረግ አለበት፡፡

7) Any public transport vehicle that has taken an exit permit from the starting station can enter and stay for up to 45 minutes at any station in the regional cities; He will have the right to stay for up to 30 minutes at stations located in zone cities.

8) It shall load the vehicle's seat and provide service according to the approved fare for the route;

9) It shall transport passengers material weighing up to 25 kg without additional charge, the loading and unloading service fee for this load shall be covered by the operator; The traveler is not obliged to pay;

10) It subject to the provision of Sub article (10) of this article, shall charge only the tariff set by the Ministry for loads of more than 25 kg;

11) It shall prepare and provide necessary resources (scales, uniforms, badges, etc.) for the deployment of the vehicles, and ensure that the employees who provide service at the station wear appropriate uniforms and badges.

12)በስምሪቱ መሠረት ጉዞ ከጀመረ በኋላ ተሽከርካሪው ቢበላሽ ወይም ተጠግኖ አገልግሎት መስጠት ባይችል ወዲያውኑ ሌላ ተሽከርካሪ በመተካት ተጓዦችን ወደ መድረሻ ቦታ ማድረስ ወይም በተጓዙ ፍላጎት መሠረት ከተከፈለው ጠቅላላ የጉዞ ክፍያ ላይ ቀሪውን የጉዞ ርቀት የሚሸፍን የጉዞ ሒሳብ በማስላት ለተጓዙ መመለስ አለበት፡፡

13)ሚኒስቴሩ ባጸደቀው የስምሪት ፕሮግራም መሠረት የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን መደልደል እና የስምሪት መስመሩን መሸፈን አለበት፡፡

14)ኦፕሬተሩ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ደረሰኝ ማሳተም እና ለተጓዦች መስጠት ወይም በቴክኖሎጂ ተደግፎ የተዘጋጀ ደረሰኝ ለተገልጋዩ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

15) የተሽከርካሪው ወንበር 50 በመቶ በተጓዦች ከተሞላና የመነሻ ሰዓቱ ከደረሰ ተሽከርካሪው ጉዞ መጀመር አለበት፡፡

16) ለተጓዦች በጉዞ ወቅት ከ0፡30 ደቂቃ እሰከ 0፡45 ደቂቃ የሚሆን የቁርስ እንዲሁም የምሳ መመገቢያ ጊዜ መስጠት አለበት፡፡

12) If the vehicle breaks down after starting the journey according to the schedule or if it is unable to provide quick repair service, it must be replaced by another vehicle and take the travelers to the destination or according to the traveler's wishes, the money paid should be returned to the traveler taking into account the remaining travel distance;

13) Sorting vehicles and cover the trip route according to the trip schedule issued by the ministry.

14) The operator Printing a receipt for providing transport services and giving it to the user or making it available to the user with the help of technology;

15) If the vehicle seat is 50% filled with passengers and the departure time is reached, the journey should start.

16) It Shall give enough time (0:30-0:45 minutes) for breakfast and lunch to the passengers during the trip.

17) ተሽከርካሪው የቴክኒክ ብልሽት ካላጋጠመው በስተቀር ተጓዦችን ከአንዱ ተሽከርካሪ ወደ ሌላ ተሽከርካሪ ማዛወር የለበትም፡፡

18) ለአገልግሎት የሚቀርቡ ተሽከርካሪዎች ንጽሕናቸው የተጠበቀና የቴክኒክ ብቃታቸው የተረጋገጠ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

19) ለተጓዥ መንገደኞች ተገቢውን ሰብዓዊ ክብርና ስለጉዞው አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ የመስጠት ኃላፊነት ያለበት ሲሆን በተለይም ደግሞ የቁርስ፣ የምሳና የማደሪያ ቦታን እና የሰዓት አጠቃቀምን ማሳወቅ አለበት፡፡

20) የኮንትራት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ኦፕሬተር በትክክለኛ መረጃ የተደገፈ ጥያቄ ለሚኒስትሩ ማቅረብና ማስፈቀድ ያለበት ሲሆን የሚጓዝበት ቦታ ከማንኛውም መናኸሪያ ቢያንስ የ3 ኪሎ ሜትር ርቀት ወሰን ውጪ መሆን አለበት፡፡

21) ትራንዚት የሚያደርግ ተሽከርካሪ ከመነሻው መነሳቱ ከተረጋገጠ የቅድመ ትኬት አገልግሎት የማግኘት እንዲሁም ባደረበት መናኸሪያ ውስጥ ከሌሊቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ ቢበዛ እስከ 45 ደቂቃ ያህል መቆየት ይችላል፡፡

17) Shall not be transferred passengers from one vehicle to another unless the vehicle has a technical breakdown.

18) Ensuring the cleanliness and technical efficiency of vehicles offered for service.

19) It shall give due respect and provide necessary information to the travelers about the general conditions of the trip, and in particular, he should inform the travelers about the location of breakfast, lunch and lodging and the use of time to traveling passengers.

20) An operator who wants to provide contract public transport services must be outside the boundary of at least 3 kilometers from any station by submitting a request supported by valid information and obtaining a permit.

21) If a transiting vehicle is confirmed to have departed from its origin, it will have the right to get advance ticket service and stay at the station it is staying at for a maximum of 45 minutes from 6:00 midnight.

31. <u>የሕዝብ ክምችት በሚኖርበት ጊዜ ስለሚሰጥ የልዩ ጉዞ ስምሪት አገልግሎት</u>

1) በአንድ መናኸሪያ ወይም መነሻ ላይ በመደበኛነት ከሚሰጠው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በላይ የሆነ ከፍተኛ የጉዞ ፍላጎት ሲኖር የልዩ ጉዞ አገልግሎት ስምሪትና መውጫ ፈቃድ በሚኒስቴሩ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2) በመደበኛ የትራንስፖርት ስምሪት አሠራር መሠረት አገልግሎት መስጠት ያልተቻለው የጉዞ መስመር ላይ ያለውን የአቅርቦት ዕጥረት ለማሟላት በራስ ተነሳሽነትና ፍላጐት በመደበኛ አሠራር አገልግሎት ለመስጠት ለሚጠይቁ ኦፕሬተሮች ቅድሚያ ፈቃድ እንዲያገኙና ወደ ጠየቁበት የጉዞ መስመር እንዲሰማሩ ይደረጋል፡፡
3) በመደበኛ አሠራር አገልግሎት ለመስጠት የሚጠይቁ ኦፕሬተሮች ስምሪት ከወሰዱ በኋላ እጥረቱ ካልተቀረፈ በቀጣይ እንደማካካሻ በመደበኛ አገልግሎት ያልተሸፈነ መስመር ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ታሳቢ በማድረግ በመደበኛ የጉዞ ታሪፍ አገልግሎት ለመስጠት ለሚፈልጉ የትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የስምሪትና መውጫ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

31. <u>Special Travel Route Services Provided When There is Public Stock</u>

1) When there is a high demand for travel beyond the regular public transport service at a destination or point of departure, a special travel route trip and exit permit may be granted.
2) In order to meet the lack of supply on the route that cannot be provided according to the normal transport deployment system, those operators who come forward voluntarily and voluntarily to provide service in the normal system will be given priority permission and deployed to the route they requested.
3) If the shortage is not resolved after the operators who request to provide services in the regular system have taken deployment, as a compensation, they will be considered to give priority to the route not covered by the regular service, and the transport operators who want to provide the service at the regular travel tariff will be given deployment and exit permits.

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተጠቀሰው አገልግሎት ሁሉንም አማራጮች አሟጦ በመጠቀም ያልተቀረፈ እንደሆነ የሕዝብ ፍሰት ችግሩን ለመቅረፍ የመደበኛ ጉዞ ክፍያ ታሪፍ ላይ 35 በመቶ ጭማሪ በማድረግ ኦፕሬተሮችን በማወዳደር አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተጠቀሰው አገልግሎት በመስጠት ያልተቀረፈ እንደሆነ የሕዝብ ፍሰት ችግሩን ለመቅረፍ ለሥራ ክፍሉ መሪ ሥራ አስፈጻሚ በማቅረብ ሲፀድቅ በመደበኛ የጉዞ ታሪፍ ላይ 50 በመቶ ጭማሪ በማድረግ ኦፕሬተሮችን በማወዳደር አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

32. አዲስ የሚከፈቱና መደበኛ ፕሮግራምወጥቶላቸው መሸፈን የማይችሉ መስመሮችን ተደራሽ ስለማድረግ

1) አዲስ የሚከፈቱ ወይም በመደበኛነት መሸፈን የማይችሉ መስመሮች የትኞቹ እንደሆኑና ስምሪት ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ በሚኒስቴሩ ሊጠና ወይም በዘርፉ በተሰማራ ኦፕሬተር ተጠንቶ ለሚኒስቴሩ ሊቀርብ ይችላል፡፡

4) If the service mentioned under sub-article 2 and 3 of this article has not been solved by exhausting all options, to overcome the problem of public flow, increase the fare of regular travel by 35 percent and compare operators to provide services.

5) If it is not solved by providing the services mentioned in sub-paragraph 4 of this article, in order to overcome the problem of public flow, when it is approved by the leading executive of the work department, by making a 50 percent increase in the standard travel fee tariff, to provide services by comparing operators.

32. Making Accessible Routes that are Newly Opened and cannot be Covered By Regular Schedule

1) Which routes are newly opened or which cannot be covered regularly and how they can be deployed can be studied by the minister or an operator engaged in the sector can be studied and presented to

2) አዲስ የሚከፈቱ ወይም በመደበኛነት መሸፈን የማይችሉ ተብለው የተለዩ መስመሮች እንዲከፈቱ ለማድረግ ሚኒስቴሩ ኦፕሬተሮችን አወዳድሮ በመመደብ ለዚህ መስመር የሚያገለግል የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች ተወዳዳሪዎች ካልቀረቡ ተቀባይነት ያለው ጥናት አጥንቶ ላቀረበ ወይም በውድድሩ ለቀረበው ኦፕሬተር ሚኒስቴሩ ሊሰጠው ይችላል፡፡

4) አዲስ የሚከፈቱ ወይም በመደበኛነት መሸፈን የማይችሉ ተብለው በተለዩ መስመሮች ላይ ለመሥራት ፈቃድ የወሰደ ኦፕሬተር በተቀመጠው ፕሮግራም መሠረት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን በየስምሪቱ የተሳፋሪ ብዛት ከተሸከርካሪው የወንበር ብዛት 25% ከተሸፈነ የማጓጓዝ ግዴታ አለበት፡፡

5) አዲስ በሚከፈቱ ወይም በመደበኛነት መሸፈን የማይችሉ ተብለው በተለዩ መስመሮች ላይ ለመሥራት ፈቃድ የወሰደ ኦፕሬተር የተሰጠው መስመር ለሁለት ዓመት እንዲቆይ የሚደረግ ሲሆን መስመሩ መደበኛ ሽፋን ካላገኘ እንደ አስፈላጊነቱ ለተጨማሪ አንድ ዓመት ፈቃዱ ሊታደስ ይችላል፡፡

the minister.

2) In order to open new routes or routes that cannot be covered regularly, the Ministry will compete and allocate operators and issue a work permit for this routes.

3) Subject to the provision of sub article (2) of this article, if no other competitors are submitted, the minister may give it to the operator who has studied and submitted an acceptable study or submitted in the competition.

4) An operator who has obtained a license to work on newly opened or designated routes that cannot be covered regularly is obliged to provide services according to the set program and is obliged to transport if the number of passengers in each route is covered by 25% of the number of seats in the vehicle.

5) An operator who takes a license to work on newly opened route or route that cannot be covered regularly, the given route will be valid for two years.

6) አዲስ በተከፈተ ወይም በመደበኛነት መሸፈን በማይችል መስመር ለመስራት ፈቃድ የወሰደው ኦፕሬተር በየወሩ ቢያንስ 15 ቀናት መስመሩን መሸፈን አለበት፡፡

7) አዲስ በተከፈተ ወይም በመደበኛነት መሸፈን በማይችል መስመር ለመሥራት ፈቃድ የወሰደው ኦፕሬተር ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መደበኛ ታሪፍ መሠረት አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመስመሩን ሁኔታ በማጥናት ሚኒስቴሩ የተለየ ታሪፍ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

33. በሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ስለሚሳፈሩ ተጓዦች

1) ማንኛውም ተጓዥ ታሪፍ ከፍሎ በተሳፈረበት ተሽከርካሪ ውስጥ አንድ መቀመጫ ወንበር ተመድቦለት ይጓዛል፡፡

2) አንድ ተጓዥ እስከ ሰባት ዓመት ዕድሜ ያለውን አንድ ሕፃን ወንበር ሳይዝ በነፃ ይዞ የመጓዝ፣ ከስምንት እስከ አሥራ ሁለት ዓመት ያለን አንድ ሕፃን ደግሞ በግማሽ ክፍያ ሕፃኑ ወንበር ይዞ ይጓዛል፡፡

3) አንድ ተጓዥ ዕድሜያቸው ከሦስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት ያሉ ሁለት ሕፃናት ይዞ የሚሳፈር ከሆነ ሁለቱ

6) An operator who has taken permission to work on a newly opened route or a route that cannot be covered regularly must cover the route for at least 15 days every month.

7) The operator who has taken permission to work on a route that is newly opened or cannot be covered regularly will provide services according to the standard tariff issued by the Ministry and when necessary, the Ministry may prepare a different tariff after studying the condition of the line.

33. Passengers who board public Transportation

1) Every passenger has the right to travel by paying a fare and having one seat assigned to him in the vehicle he boarded;

2) A passenger has the right to travel with one child up to seven years of age (without a seat) for free, and one child between eight and twelve years of age with a half-paying seat.

3) If a passengers is traveling with two children between the ages of 3 and 7 years old, they will be charged the full fare of one person

ሕፃናት አንድ ወንበር ይዘው የአንድ ሰው ሙሉ ክፍያ ይከፍላል፡፡

4) ተጓዡ ዕድሜያቸው ከሦስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት ያሉ ሦስት ሕፃናት ይዞ የሚሳፈር ከሆነ ሦስቱ ሕፃናት ሁለት ወንበር ይዘው የሁለት ሰው ሙሉ ክፍያ ይከፍላል፡፡

5) አንድ ተሽከርካሪ ካለው የወንበር ብዛት 10% ያህሉን በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (2) እስከ (4) በተመለከተው አግባብ ሕፃናትን ማሳፈር አለበት፡፡

6) የትራንስፖርት ድርጅቱ ተረክቦ የጫናቸውን ዕቃዎች ሲጫኑ፣ በጉዞ ወቅት ወይም ጉዞው መጨረሻ ላይ ሲወርዱ ለሚደርስባቸው ጉዳት፣ ብልሽት እና መጥፋት ሙሉ ኃላፊነቱን ወስዶ የማካካሻ ክፍያ የመፈጸም ወይም የመተካት ግዴታ አለበት፡፡

7) ማንኛውም ተጓዥ ንዙን በማስመዘንና ለኦፕሬተሩ ሠራተኞች በማስረከብ ከኦፕሬተሩ ሠራተኞች የሚሰጠውን የዕቃ ታግ ንዙን መልሶ እስኪረከብ ድረስ እስከ ጉዞው መጨረሻ መያዝ አለበት፡፡

8) ማንኛውም ተጓዥ ለጉዞ በተዘጋጀው ተሽከርካሪ ውስጥ በመግባት በትኬቱ ላይ በተመለከተው የወንበር ቁጥር መሠረት መቀመጥ አለበት፡፡

for the two children;

4) If the Passenger is traveling with 3 children between the ages of 3 and 7 years old, the three children will be charged the full fare of two people; The children will travel with the same seat as the fare they paid.

5) About 10 percent of the number of seat in a vehicle shall be child restraints in accordance with sub article (2) to (4) of this article.

6) When the transport company takes over and loads the goods they have loaded; takes full responsibility for any damage, breakdown or loss incurred during the trip or when disembarking at the end of the trip and is obliged to pay compensation or replace it;

7) Any passengers shall keep the baggage tag provided by the operator's staff after weighing the bag and handing it over to the operator's staff until the end of the trip.

8) Every passenger must enter the vehicle prepared for the trip and sit according to the seat number on the ticket.

9) በጉዞ ወቅት የጉዞ ትኬት የጠፋባቸው ወይም የተቀደደባቸው ተሣፋሪዎች በቀሪ ትኬት መረጃ ያለተጨማሪ ክፍያ ይጓዛሉ፡፡

10) ተጓዡ ጉዞውን የሰረዘው መሆኑን ለኦፕሬተሩ ወይም ትኬቱን ለሸጠለት አካል ከሁለት ሰዓት በፊት ካስታወቀ የከፈለው ክፍያ 30 በመቶ ተቀናሽ ሆኖ ይመለስለታል፡፡

11) ተጓዡ ጉዞውን የሰረዘው መሆኑን ለኦፕሬተሩ ወይም ትኬቱን ለሸጠለት አካል ከጉዞው ቀን ጀምሮ እስከ 3ኛው ቀን ድረስ ካሳወቀ ከከፈለው ክፍያ ላይ 50 በመቶ ተቀናሽ ሆኖ ይመለስለታል፡፡

12) ከጉዞው ቀን ጀምሮ ከ3ኛው ቀን በኋላ የክፍያ ይመለስልኝ ጥያቄ የሚያቀርብ ተጓዥ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

13) ተሽከርካሪው በቲኬቱ ላይ ከተቀመጠው የመውጫ ሰዓት ከመድረሱ በፊት ቀድሞ ከወጣ ተሳፋሪው የከፈለውን ገንዘብ በሙሉ ከ10 በመቶ ተጨማሪ የካሳ ክፍያ ጋር ይመለስለታል፡፡

14) ከሕፃናት ዕድሜ ጋር ተያይዞ ለሚነሱ አለመግባባቶች ከሕጋዊ አካል የተሰጠውን ማረጋገጫ በማቅረብ አገልግሎቱን ማግኘት ይቻላል፡፡

9) Passengers whose payment receipt is lost or torn during the trip have the right to travel without additional payment with the remaining receipt information.

10) If the passenger informs the operator or the person who sold the ticket that he has canceled the trip two hours before the start of the trip, the company shall refund to the passenger with a 30 percent deduction.

11) If the passenger informs the operator or the person who sold the ticket that he has canceled the trip up to 3 days from the start of the trip, the company shall refund to the passenger with a 50 percent deduction.

12) Late refund request after 3 days including the date of travel shall not be accepted.

13) If the vehicle leaves before the departure time specified on the ticket, the passenger will be refunded the entire amount paid with an additional 10% compensation.

14) For disputes related to the age of children, the service can be obtained by providing the confirmation from the legal entity.

34. ልዩ ድጋፍ ስለ ሚያስፈልጋቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች

1) ማንኛውም ሰው ወይም ኦፕሬተር ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን ድጋፍ የማድረግና በማንኛውምየትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ቅድሚያ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፡፡
2) ማንኛውም ኦፕሬተር በስሩ ያሉትን ተሽከርካሪዎች ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ምቹ የማድረግ፣ በቀላሉ ወደ ተሽከርካሪዎቹለመውጣትና ለመውረድ የሚያስችል ዊልቸር እና ሊፍት እንዲኖረው የማድረግ እና ከአሽከርካሪው በስተኋላ ባሉ ተከታታይወንበሮች ላይ እንዲቀመጡ ማድረግ አለበት፡፡
3) ማንኛውም ሰው ወይም ኦፕሬተር ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች መረጃ ሲጠይቁ መረጃ በመስጠት፣ ዕቃቸውን በመያዝና የዝርፊያ እና የስርቆት ወንጀል ሰለባ እንዳይሆኑ ተገቢውን ትብብር ማድረግ አለበት፡፡
4) ማንኛውም ኦፕሬተር መስማት ለተሳናቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች እና ለዓይነ ስውራን በምልክት እና በድምፅ መረጃ ሊሰጥ የሚያስችል መሣሪያ

34. About The Sections Of Society That Need Special Support

1) Any person or operator must provide appropriate support to the members of society who need special support and ensure that they get priority service on any transport service.
2) A vehicle engaged in public transport service must be made comfortable for members of the public who need special support, have a wheelchair and elevator to easily get on and off the vehicle, and make them sit on a series of seats behind the driver.
3) Any person or operator who needs special support is obliged to provide information when they ask for information, to support them by holding their belongings, so that they do not become victims of robbery and theft.
4) Any operator must keep a device in the vehicle that can provide information to the deaf community by sign and by voice to the blind community.

በተሽከርካሪው ውስጥ ማስቀመጥ አለበት፡፡

ክፍል አምስት
የአደረጃጀት እና የሀብት ሽግግር ሂደት አፈጻጸም

35. የአደረጃጀት እና የሽግግር ሂደት አፈጻጸም

1) በቀድሞ የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 መሠረት ፈቃድ ወስደው በሥራ ላይ የሚገኙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 መሠረት ተሽከርካሪዎቻቸውን በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት እንደገና በማስመዝገብ አዲስ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መውሰድ አለባቸው፡፡
2) በቀድሞ የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 መሠረት የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወስደው በሥራ ላይ የሚገኙ የትራንስፖርት ማኅበራት አግባብነት ባለው የንግድ ሕግ መሠረት በንግድ አደረጃጀት ተመዝግበውና ተገቢውን የንግድ ፈቃድ ይዘው በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን መስፈርት በማሟላት አዲስ በተመዘገቡበት የአክስዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የግል

Part Five
Implementation of the Process of Organization and Asset Transfer

35. Implementation of Organization and Transition Process

1) Individuals or organizations who have obtained a license in accordance with the previous Transport Proclamation No. 468/2005 shall be re-register their vehicles in accordance with the requirements set forth in this directive and obtain a new operator's competency assurance license in accordance with the Road Transport Proclamation No. 1274/2022.
2) Associations who have obtained a license in accordance with the previous Transport proclamation No. 468/2005 shall have commercial business license in accordance with the relevant commercial law and shall obtain new operator's competency license in the name

ትራንስፖርት ስም አዲስ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መውሰድ አለባቸው።።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት እንደገና ተመዝግበው የኦፕሬተርነት ፈቃድ መውሰድ ያለባቸው ይህ መመሪያ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ዕለት ጀምሮ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ይሆናል።።

4) በዚህ አንቀጽ መሠረት እንደገና ምዝገባ አድርገው አዲስ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያልወሰዱ ኦፕሬተሮች በንዑስ-አንቀጽ (3) ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በኋላ ቀድሞ የነበራቸው የኦፕሬተርነት ፈቃድ ይሰረዛል።።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አዲስ በሚለወጡበት የንግድ አደረጃጀት መሠረት ምዝገባ አድርገው አዲስ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ያልወሰዱ ማኅበራት በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3) ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በኋላ ሕጋዊ ሰውነት አይኖራቸውም።።

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (4) እና (5) መሠረት የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ የተሰረዘና ሕጋዊ ሰውነቱን ያጣ ግለሰብ ወይም

of a share company or a private limited company or a private transport by fulfilling the requirements set out in this directive.

3) The operator competency license under sub Article (2) of this Article shall be obtained within /thirty/ 30 working days from the effective date of this directive.

4) Operators who have not re-registered and obtained operator's competency license, their previous operator's license shall be canceled after the time set under sub Article (3) of this Article.

5) Associations shall not have any legal personality as of the time set under sub Article (3) of this Article if they do not registered to the newly established business organization and obtain an operator's competency license in accordance with sub Article (2) of this Article.

6) The relevance law shall be applicable for Individual or company or association whose operator competency license

ድርጅት ወይም ማኅበር ቀደም ሲል ከ3ኛ ወገን ጋር የነበረው የውል ወይም ሌላ ዓይነት ግንኙነት አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

36. የማኅበራት የሀብት ሽግግር ሂደት አፈጻጸም

1) በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 መሠረት ተቋቁመው በመሥራት ላይ የነበሩ የትራንስፖርት ማኅበራት ያላቸውን ሀብትና ንብረት በገለልተኛ የተመሰከረለት የሒሳብ ባለሙያ በማስመርመር በጠቅላላ ጉባኤው ማጸደቅ አለባቸው፡፡

2) በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 መሠረት ተቋቁመው በመሥራት ላይ የነበሩ ማኅበራት ፈርሰው ያላቸው ሀብት እና ንብረት በአዲስ ወደ ሚቋቋሙበት የንግድ ድርጅት በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች መሠረት ይተላለፋል፡፡

3) ከማኅበር ወደ ንግድ ድርጅት የሚተላለፈው ሀብትና ንብረት ለማኅበሩ አባላት በግል ማከፋፈል የተከለከለ ነው፡፡

cancelled in accordance with sub Article (4) and (5) in relation to its relation with third parties.

36. Implementation of the Process of Transfer of Assets of Associations

1) Assets and property of the transport associations that were established and operating in accordance with the Transport Proclamation No. 468/2005, shall be audited by external auditors and approved by the members in the general assembly.

2) Assets and property of associations that were established in accordance with Proclamation No. 468/2005, and that dissolved will be transferred to the newly established business organization.

3) The assets and property transferred from the association to the business organizations shall not be distributed to the members of the association individually.

4) የቀድሞው ማኅበር የሀብት እና ንብረት ዝውውር የሚመለከታቸው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት በሚደረገው የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ጊዜ በማኅበሩ ስር ታቅፈው የሚገኙ አባላትን እና አዲስ በተቋቋመው የንግድ ድርጅት ውስጥ ባለድርሻ ሆነው የቀጠሉ አባላትን ብቻ ነው፡፡

5) በአዋጁ አንቀጽ 11 (7) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት የማኅበሩን ሀብት እና ንብረት አዲስ ወደሚቋቋመው የንግድ ድርጅት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ (3) በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ማስተላለፍ ካልተቻለ አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

6) በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 መሠረት ተቋቁመው በመሥራት ላይ የነበሩ ማኅበራት ከሌላ ሦስተኛ ወገን ጋር የነበራቸው መብትና ግዴታ በዚህ መመሪያ መሠረት ከተመዘገቡበት ዕለት ጀምሮ አዲስ ወደተመሰረተው የንግድ ድርጅት የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

4) The transfer of assets and property under sub Article (1) and (2) of this Article is only applicable to the members who were already members of the association during this transition period and those who continue to be shareholders in the newly established business organization.

5) According to Article 11 (7) of the Proclamation and under sub Article (2) and (3) of this Article, if the assets and property of the association cannot be transferred to the newly established business organization within the time period set under sub Article (3) of Article 42, the civil code of the country shall be applicable on such matters.

6) According to Proclamation No. 468/2005, the rights and obligations of associations that were established and working with other third parties shall be transferred to the newly established business organization starting from the date of registration.

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተመለከተው ድንጋጌ የማኅበር አባላት በግል ከሌላ ሦስተኛ ወገን ጋር ያላቸው የመብትና ግዴታ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

37. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

ለማንኛውም ኦፕሬተር የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡

1) የሌላ ኦፕሬተርን አርማና ስቲከር በማንኛውም ሁኔታ መገልገል፤
2) ለሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ተባባሪ መሆን እና ስደተኞችን በተሸከርካሪው ደብቆ ማጓጓዝ፤
3) የኮንትሮባንድ ዕቃ ማጓጓዝ፣ ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ይዞ መገኘት፤
4) ባልተመዘገቡ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ባልወሰዱ ወይም ባላደሱ ወይም በታገዱ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት መስጠት፤
5) ትክክለኛ ያልሆኑና ሐሰተኛ መረጃዎችን እና ሰነዶችን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤
6) ከሚኒስቴሩ የተፈቀደለትን ስቲከርና ሌሎች ከኦፕሬተርነት ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት፤
7) ሌሎች ሕገ-ወጥ ተግባራትን መፈጸም፤

7) The provisions of Article 6 of this Article shall not apply to the rights and obligations of the members of the association with other third parties.

37. <u>Prohibited Activities</u>

Any operator shall be prohibited from engaging in the activities listed below.

1) Using in any manner other operators logos and stickers.
2) Being an accomplice to illegal human trafficking and smuggling refugees in the vehicle.
3) Transporting contraband and possessing illegal weapons;
4) Providing services with vehicles that are not registered; have not received or renewed a competency assurance license or vehicles that are suspended.
5) Providing inaccurate and false information and documents to the ministry;
6) Handing over sticker and other permits related to operatorship to another person.
7) Collaborating with other illegal activities and practices.

38. በሌሎች ሕጎች መሠረት የትራንስፖርት አገልግሎት ስለሚሰጡ ድርጅቶች

1) ማንኛውም በሌላ ሕግ የተቋቋመ ድርጅት የተቋቋመበት ዓላማ ሌላ አገልግሎት ለመስጠት ሆኖ ይህ አገልግሎት በማይኖርበት ጊዜ ማንኛውንም የሕዝብ ትራንስፖርት ገልግሎት በመስጠት ተግባር መሠማራት እንደሚችል በተቋቋመበት ሕግ ላይ ከተመለከተ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከሚኒስቴሩ መውሰድ ሳይጠበቅበት በሀገር ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ የትራንስፖርት አገልግሎቱን ከሀገር ውጭ ጭምር ድንበር በመሻገር መስጠት ከፈለገ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መውሰድ ሳያስፈልገው በድርጅቱ ጠያቂነት ድርጅቱን በመመዝገብ ብቻ የውጭ ሀገር መግቢያና መውጪያ ፈቃድ ከሚኒስቴሩ ሊሰጠው ይችላል፡፡

38. Organizations engage in Public Transport service by other laws

1) Any organizations established by another law, the purpose of which it was established is to provide another service, when this service is not available, it can perform any activity by providing public transport service, if it is stated in the laws under which it was established; it can provide transport services without having to obtain an operator's qualification certificate from the ministry.
2) Subject to the provisions of sub article (1) of this article, if the organization wants to provide its transportation services outside the country by crossing the border, without the need to obtain an operator's qualification certificate, it may be granted cross border entry permit by the ministry just by registering the organization at the request of the organization.

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

39. የአሠራርና የሥነ-ምግባር ጉድለት የቅጣት አወሳሰን

በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የወጡ ሌሎች ሕጎችና ደንቦች ተፈፃሚነታቸው ተእንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ የተመለከተውን አጠቃላይ የአሠራር እና ሥነ-ምግባር ጉድለቶችን በመፈጸም ኃላፊነትና ግዴታን በትክክል ባልተወጣ ማንኛውም በዚህ መመሪያ የተመለከተውን አጠቃላይ የአሠራር እና ሥነ-ምግባር ጉድለቶችን በመፈጸም ኃላፊነትና ግዴታን በትክክል ባልተወጣ ማንኛውም አጓሬተር ላይ የሚወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

40. የአስተዳደራዊ ቅጣት እርከን

1) በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩት የአሠራር እናሥነ-ምግባር ግድፈቶች በተሽከርካሪ ባለንብረቶች፣ አሽከርካሪዎች፣ በድርጅቱ ሠራተኞች ለሚፈፀሙ የሥነ-ምግባር ጉድለቶች አጓሬተሩ ኃላፊ ይሆናል፡፡

Part Six

Miscellaneous provisions

39. Determining Administrative measures for disciplinary offense

Without prejudice to the applicability of other laws and regulations issued by the relevant body, the administrative measures taken against against freight transport operator; who does not fulfill the responsibilities and obligations properly by breaching of the general procedural and committing disciplinary offenses mentioned in this directive; shall be carried out in accordance to Schedule "C" attached to this directive.

40. Level of Administrative Measures

1) If the disciplinary violations listed under this directive are found committed by the company's vehicles, drivers and employees, the licensed operator shall be held responsible.

2) ማንኛውም የሕዝብ ትራንስፖርት ድርጅት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ሐ" በእርከን አንድ እና ሁለት ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን ፈፅሞ ከተገኘ፡-

41. በዕርከን አንድ ለተዘረዘሩ ጥፋቶች የሚወሰድ አስተዳደራዊ ዕርምጃ

1) ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤
2) ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 30 ነጥብ ከደረሰ ከማንኛዉም አገልግሎት ጥፋቱ የተፈጸመበት የኦፕሬተሩ ተሽከርካሪ ለአንድ ወር ከሥራ ይታገዳል፡፡
3) ለሦስተኛ ጊዜ ከሆነ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 50 ነጥብ ከደረሰ ከማንኛውም አገልግሎት ጥፋቱ የተፈጸመበት የኦፕሬተሩ ተሽከርካሪ ለሦስት ወር ከሥራ ይታገዳል፡፡
4) ለአራተኛ ጊዜ ከሆነ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 70 ነጥብ ከደረሰ ጥፋቱ የተፈጸመመበት የኦፕሬተሩ ተሽከርካሪ ለስድስት ወራት ከሥራ ይታገዳል፡፡
5) ከድርጊቱ ሳይታረም በዚሁ ከቀጠለ ወይም የጥፋቱ ሪከርድ 90 ነጥብ ከደረሰ የኦፕሬተሩ ተሽከርካሪ ለአንድ ዓመት ከሥራ ይታገዳል፡፡

2) If any freight transport company is found to have committed any one of the following offenses under schedule "C" first category and second category:

41. Administrative measure for offenses Listed under first category

1) If it is the first time, a written warning will be given.
2) If it is the second time or if the offense record reaches 30 points, the vehicle of the company in which the offense was committed shall be suspended from any service for one month.
3) If it is the third time or if the offense record reaches 50 points, the vehicle of the company in which the offense was committed shall be suspended from any service for three month.
4) If it is for the fourth time or if the offense record reaches 70 points, the vehicle of the company where the offense was committed shall be suspended for six months;
5) If the act continues uncorrected or the offense record reaches 90 points, the company's vehicle shall be suspended for one year;

42. በዕርከን ሁለት ለተዘረዘሩ ጥፋቶች የሚወሰድ አስተዳደራዊ ዕርምጃ

1) ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡
2) ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 20 ነጥብ ከደረሰ ጥፋቱ የተፈጸመበት የኦፕሬተሩ ተሽከርካሪ ከማንኛውም አገልግሎት ለአንድ ወር ከሥራ ይታገዳል፡፡
3) ለሦስተኛ ጊዜ ከሆነ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 40 ነጥብ ከደረሰ ጥፋቱ የተፈጸመበት የኦፕሬተሩ ተሽከርካሪ ከማንኛውም አገልግሎት ለሦስት ወር ከሥራ ይታገዳል፡፡
4) ለአራተኛ ጊዜ ከሆነ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 60 ነጥብ ከደረሰ ጥፋቱ የተፈጸመመበት የኦፕሬተሩ ተሽከርካሪ ለስድስት ወራት ከሥራ ይታገዳል፡፡
5) ከድርጊቱ ሳይታረም በዚሁ ከቀጠለ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 80 ነጥብ ከደረሰ የድርጅቱ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ለ3 ወራት ከሥራ ይታገዳል፡፡
6) ማንኛውም ኦፕሬተር በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት አስቸኳይ ለሆኑና ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ለሆኑ በመንግሥት ለሚሰጡ ትእዛዞች አለመተባበር፣ ወይም ሕገ-ወጥ

42. Administrative measure for offenses Listed under second category

1) If it is the first time, a written warning will be issued;
2) If it is for the second time or if the violation record reaches 20 points, the vehicle of the organization where the violation occurred shall be suspended from any service for one month;
3) If it is for the third time or if the offense record reaches 40 points, the company vehicle where the offense occurred shall be suspended from any service for three months;
4) If it is for the fourth time or if the violation record reaches 60 points the vehicle of the company where the violation occurred shal be suspended for six months;
5) If the action continues without correction or if the violation record reaches 80 points, the company's competency certificate will be suspended from business for 3 months.
6) Failure to cooperate with national special operations for various reasons, or being an accomplice

Habtamu Hailemeskel- Legal Consultant & Attorney

የሰዎች ዝውውር፣ ወይም የኮንትሮባድ ዕቃ ማጓጓዝ፣ ወይም ሕገ-ወጥ የጠር መሣሪያ ይዞ መገኘት ወይም ወደ ጎረቤት ሀገር ይዞ መግባት ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ የኦፕሬተሩ ተሽከርካሪዎች በቀጥታ ለ6 ወራት ከሥራ ይታገዳል፡፡

to human trafficking, or transporting contraband goods, or possessing illegal weapons, or transporting in to neighboring country, the operator vehicles shall be suspended for 6 months unconditionall.

43. የቅሬታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት

1) በመመሪያው መሠረት በተሰጠው አገልግሎት ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል ቅሬታውን አገልግሎቱን ለሚሰጠው የዘርፉ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ቅሬታው በተፈጠረ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2) የዘርፉ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ለቀረበው ቅሬታ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡
3) የዘርፉ መሪ ሥራ አስፈጻሚ በሰጠው ምላሽ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ በበላይነት ዘርፉን ለሚመራው ሚኒስትር ዴኤታ ማቅረብ ይችላል፡፡
4) ዘርፉን በበላይነት የሚመራው ሚኒስትር ዴኤታ ለቀረበው ቅሬታ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

43. Complaint Review Procedure

1) Any person who is dissatisfied with the service provided according to the Directive should submit the complaint in writing to the chief executive officer within 10 working days.
2) The chief executive officer must respond in writing to the complaint within 5 working days.
3) A person who has a complaint with the response of the chief executive officer should submit the complaint in writing to the state minister within 3 working days.
4) The state minister responds in writing to the complaint within 10 days.

5) ዘርፉን በበላይነት በሚመራው ሚኒስትር ዴኤታ በተሰጠው ምላሽ ቅር የተሰኘ ሰው በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለሚኒስትሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

6) ሚኒስትሩ ለቀረበው ቅሬታ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል።

44. <u>የአገልግሎት ክፍያ</u>

1) ማንኛውም ኦፕሬተር በዚህ መመሪያ መሠረት በየደረጃው የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እና የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት በመንግሥት የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

2) ማንኛውም ተሽከርካሪ ከመናኸሪያ ስምሪት ተሰጥቶት በወጣ ቁጥር የመናኸሪያ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡

45. <u>የተሻሩ መመሪያዎች</u>

በቀድሞ የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ጸድቀው በስራ ላይ ከነበሩት ውስጥ የሚከተሉት መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

1) በብቸኝነት የሚሰጡ መስመሮችን በተመለከተ የተዘጋጀ የአሠራር ሥርዓት የተሻሻለ መመሪያ ቁጥር 672/2013፤

5) A person who has a complaint with the response of the state minister should submit the complaint in writing to the minister within 3 working days.

6) The Minister responds in writing to the complaint within15 working days**;** the response to the complaint by the Minister will be the final administrative decision.

44. <u>Service Fee</u>

1) Every person has to pay the prescribed service fee to obtain operator competency license and various services as per this directive.

2) Any vehicle has to pay the public transport terminal fee each time after having trip from the terminal.

45. <u>Repealed Directive</u>

The following Directives previously approved by the Federal Transportation Authority are repealed by this Directive:

1) Revised Directive No. 672/2013 on the operating system for Exclusive route;

2) በሀገር አቋራጭ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የቁርስ፣ የምሳና የማደሪያ ቦታዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 673/2013፤

3) ከመደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት በላይ ከፍተኛ የሕዝብ ክምችት ሲኖር ስለሚሰጥ የጉዞ ፈቃድ የተዘጋጀ የአሠራር መመሪያ ቁጥር 674/2013፣

4) የሕዝብ ትራንስፖርት ማመላለሻ የጉዞ መመሪያ ቁጥር 675/2013፤

5) የተሻሻለ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና ሥምሪት የሥራ ሂደት የሥምሪት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 676/2013፤

6) የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የአሠራር መመሪያ ቁጥር 677/2013፤

7) በሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ለተሰማሩና ለተደራጁ የትራንስፖርት ማኅበራትና ድርጅቶች በ2003 ዓ.ም ተሻሽሎ የተዘጋጀ መተዳደሪያ ደንብ (ሞዴል) ቁጥር 679/2013፤

8) በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህኅብረተሰብ ክፍሎች የወጣ መመሪያ ቁጥር 680/2013፤

2) Directive No. 673/2013 issued to determine breakfast, lunch and accommodation areas in cross-country public transport services;

3) Directive No. 674/2013 prepared for travel permits issued when there is a large crowd over normal public transport;

4) Public Transport Travel Directive No. 675/2013;

5) Public Transport Service Competency Assurance and Trip Implementation as Amended Directive No. 676/2013;

6) Public Transport Service Delivery Operating Instructions No. 677/2013;

7) Memorandum of Association (Model) Model No. 679/2013, prepared for Enterprise and associations engaged in public transportation as revised in 2003;

8) Directive No. 680/2013 issued to Sections of Society In Need Of Special Support;

Habtamu Hailemeskel- Legal Consultant & Attorney

46. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡

47. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሚኒስቴሩ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

48. አባሪ ሰነዶች

ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዙ ሰነዶችና ቅጾች የዚህ መመሪያ አካል ናቸው፡፡

49. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ጥር_2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር)
የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ
ሚኒስቴር
ሚኒስትር

46. Inapplicable Directives

Any customary practices and other Directive contradictory of this directive shall not be applicable to matters covered under this Directive.

47. Amendment of the Directive

The Minister may amend this directive as it deems necessary.

48. Attachment Documents

The documents and forms attached to this directive are part of this directive.

49. Effective Date of the Directive

This directive shall be effective from the day it is registered by the Ministry of Justice and uploaded on its website.

January, 2024
Addis Ababa

Alemu Sime (Phd.)
Minister
Ministry of Transport and Logistics

ሠንጠረዥ-"ሀ"

የሕዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች ዝቅተኛ የሰው ኃይል አደረጃጀት

ተ.ቁ	የስራ መደብ	አክሲዮን				ኃላ/የተ/የግ/ማህበር				ግል ትራንስፖርት			
		ልዩ	ደረጃ 1	ደረጃ 2	ደረጃ 3	ልዩ	ደረጃ 1	ደረጃ 2	ደረጃ 3	ልዩ	ደረጃ 1	ደረጃ 2	ደረጃ 3
1	ዋና ሥራ አስኪያጅ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
2	የኦፕሬሽንና የስምሪት ኃላፊ	1	1	1	-	1	1	-	-	1	-	-	-
3	የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ	1	1	1	1	1	1	-	-	1	-	-	-
4	የሂሳብ ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
5	የኮምፒውተር /አይሲቲ ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	-	-	1	-	-	-
6	የመንገድ ደኅንነት ባለሙያ	1	1	-	-	1	1	-	-	1	1	-	-

Schedule "A"

Public Transport Operators Minimum Man Power Structure

No	Position	share company				Private Limited Company				Private transport			
		Special	Level 1	Level 2	Level 3	Special	Level 1	Level 2	Level 3	Special	Level 1	Level 2	Level 3
1	General manager	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
2	Head of Operations and Trip	1	1	1	-	1	1	-	-	1	-	-	-
3	Head of Administration and Finance	1	1	1	1	1	1	-	-	1	-	-	-
4	Accountant	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
5	Computer /ICT specialist	1	1	1	1	1	1	-	-	1	-	-	-
6	Road safety expert	1	1	-	-	1	1	-	-	1	1	-	-

ሠንጠረዥ-"ለ"

ለሁሉም የኦፕሬተር ዓይነቶች ተፈላጊ ሰው ኃይል፣ የትምህርት ደረጃ፣ የትምህርት ዓይነት እና የስራ ልምድ፡-

ተ.ቁ	የስራ መደቡ መግለጫ	የትምህርት ደረጃ	የትምህርት ዓይነት	የስራ ልምድ
1	ዋና ሥራ አስኪያጅ	ማስተር ዲግሪ ዲፕሎማ	በትራንስፖርት ፕላኒንግና ማኔጅመንት ወይም በትራንስፖርት ኢንጅነሪንግ ወይም በአርባን ትራንስፖርት ወይም በትራንስፖርት ሳይንስ ወይም በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ ወይም በኢኮኖሚክስ ወይም በሊደርሺፕ ወይም በሎጂስቲክስ ወይም በቢዝነስ አስተዳደር ወይም በቢዝነስ ማኔጅመንት ወይም በማኔጅመንት ወይም በተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ	1/2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ
2	የኦፕሬሽን ና የስምሪት ኃላፊ	ማስተር ዲግሪ ዲፕሎማ	በትራንስፖርት ፕላኒንግና ማኔጅመንት ወይም በትራንስፖርት ኢንጅነሪንግ ወይም በትራንስፖርት ኦፕሬሽን ወይም በአርባን ትራንስፖርት ወይም በትራንስፖርት ሳይንስ ወይም በትራንስፖርትኢኮኖሚክስ ወይም በኢኮኖሚክስ ወይም በሊደርሺፕ ወይም በሎጂስቲክስ ወይም በቢዝነስአስተዳደር ወይም በቢዝነስ ማኔጅመንት ወይም በማኔጅመንትወይም በማርኬቲንግ ወይም በአካውንቲንግና ፋይናንስ ወይም በተዛማጅየትምህርትዘርፍ	1/2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ
3	የአስተዳደርና ፋይናንስ	ማስተር ዲግሪ	በኢኮኖሚክስ ወይም በቢዝነስ አስተዳደር ወይም በቢዝነስ ማኔጅመንት ወይም በማኔጅመንትወይም በማርኬቲንግ ወይም በአካውንቲንግ ወይም	0/2/4 ዓመትእና ከዚያ

	ኃላፊ፡	ዲፕሎማ	በአካውንቲንግና ፋይናንስ ወይም በተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ	በላይ
4	የሂሳብ ባለሙያ	ዲግሪ ዲፕሎማ	በአካውንቲንግ ወይም በአካውንቲንግና ፋይናንስ ወይም በኢኮኖሚክስ ወይምበቢዝነስ አስተዳደር ወይም በቢዝነስ ማኔጅመንት ወይም በማኔጅመንት ወይም በባንኪንግና ፋይናንስ ወይም በተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ	0/2 ዓመትእና ከዚያበላይ
5	የኮምፒውተር /የአይሲቲ/ ባለሙያ	ዲግሪ ዲፕሎማ	በኮምፒውተር ሳይንስ፣ በአይ.ሲ.ቲ፣ በሳይበር ሴኩሪቲ፣ በጂ.አይ.ኤስ. እና በሌላ ከቴክኖሎጂ ጋር ተዛማጅ በሆነ የትምህርት ዘርፍ፣	0/2 ዓመት እና ከዚያ በላይ
6	የመንገድ ደህንነት ባለሙያ፡	ዲግሪ ዲፕሎማ	በትራንስፖርት ፕላኒንግና ማኔጅመንት ወይም በትራንስፖርት ኢንጅነሪንግ ወይም በትራፊክ ኢንጅነሪንግ ወይም በትራንስፖርት ኦፕሬሽን ወይም በአርባን ትራንስፖርት ወይም በትራንስፖርት ሳይንስ ወይም በሲቪል ኢንጂነሪንግ፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ ወይም በኢኮኖሚክስ ወይም በቢዝነስ አስተዳደር ወይም በቢዝነስ ማኔጅመንት ወይም በማኔጅመንት ወይም በሳይኮሎጅ ወይም በተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ	0/2 ዓመትእና ከዚያበላይ

Schedule "B"

Required Man Power, Educational qualification level, Field of study and work experience for all type of Operator

No	Position	Educational Qualification level	Field of Study	work experience
1	General manager	Master Degree Diploma	in Transportation Planning and Management or Transportation Engineering or Urban Transportation or Transportation Science or Transportation Economics or Economics or Leadership or Logistics or Business Administration or Business Management or Management or related discipline	1/2/4 years and above
2	Head of Operations and Trip	Master Degree Diploma	in Transportation Planning and Management or Transportation Engineering or Transportation Operations or Urban Transportation or Transportation Science or Transportation Economics or Economics or Leadership or Logistics or Business Administration or Business Management or Management or Marketing or Accounting and Finance or a related field of study	1/2/4 years and above
3	Head of	Master	in Economics or Business Administration or	0/2/4 years

	Administration and Finance:	Degree Diploma	Business Management or Management or Marketing or Accounting or Accounting and Finance or related discipline	and above
4	Accountant	Degree Diploma	in Accounting or Accounting and Finance or Economics or Business Administration or Business Management or Management or Banking and Finance or related discipline	0/2 years and above
5	Computer/ICT/ expert	Degree Diploma	In Computer Science, ICT, Cyber Security, GIS and in another technology-related discipline;	0/2 years and above
6	Road Safety Specialist:	Degree Diploma	in Transport Planning and Management or Transport Engineering or Traffic Engineering or Transport Operations or Urban Transport or Transport Science or Civil Engineering, Transport Economics or Economics or Business Administration or Business Management or Management or Psychology or related discipline	0/2 years and above

ሠንጠረዥ -"ሐ"

የሥነ-ምግባር ጉድለቶች እና የአስተዳደራዊ እርምጃዎች አወሳሰድ

1) በዕርከን አንድ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚያስወስዱ የጥፋት ዓይነቶች

ተ.ቁ	የጥፋት አይነቶች ዝርዝር	ለጥፋቱ የተሰጠው ክብደት
1.	ኦፕሬተሩ አስፈላጊ መረጃዎችን በተሟላ ሁኔታ አደራጅቶ አለመያዝ እና ሲጠየቅ ትክክለኛ መረጃ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ አለመስጠት፤	7
2.	ሚኒስቴሩ ባወጣው የደረጃ መስፈርት መሰረት የድርጅቱን ስም፣ አርማ እና ደረጃ የያዘ ስቲከር በተሸከርካሪዎች ሁለት ጎን አለመለጠፍ	15
3.	የተሸከርካሪውን የአገልግሎት ምዘና ውጤት የሚያሳይ ዲስክ ወስዶ በተሸከርካሪዎች ላይ አለመለጠፍ፤	20
4.	ኦፕሬተሩ አድራሻ ሲቀይር በ15 ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ አለማሳወቅ	10
5.	የተሸከርካሪዎች እንቅስቃሴ መቆጣጣሪያ መሣሪያ ብልሽት ሲገጥመው አለማሳወቅ እና አለማስተካከል፣	15
6.	ተሸከርካሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጭ በሚሆኑበት ጊዜ ያለማሳወቅ፣	20
7.	የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ለዕይታ በሚያመች መልኩ አለማስቀመጥ፣	6
8.	ከተገልጋዮች ለሚቀርቡ ቅሬታና አቤቱታዎች ተገቢ ምላሽ በወቅቱ አለመስጠት፤	7

Schedule "C"

Disciplinary offenses and Administrative measures

1) First category of offenses that result Administrative Measures

No	List of offense type	Weight of the offense
1.	Failure by operator to organize the necessary information in a complete manner and to provide accurate information when requested	7
2.	Failure to affix stickers containing the company's name, address and logo on both sides of vehicles according to the standards issued by the ministry.	15
3.	Failure to take a disc showing the vehicle's service assessment results and affix it to vehicles;	20
4.	Failure to notify the ministry within 15 days when the operator changes address	10
5.	Failure to notify and repair when a vehicle's route control device malfunctions;	15
6.	Failure to notify when vehicles are out of service for various reasons	20
7.	Failure to display the operator's qualification certificate in a visible manner;	6
8.	Failure to provide timely response to customer complaints and appeals;	7

2) በዕርከን ሁለት አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚያስወስዱ የጥፋት ዓይነቶች

ተ.ቁ	የጥፋት አይነቶች ዝርዝር	ለጥፋቱ የተሰጠው ክብደት
1.	የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን በየዓመቱ በመመሪያው መሰረት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ በወቅቱ አለማሣደስ፣	8
2.	የድርጀቱን የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ለመከታተል የተዘረጋውን ስርዓት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለቁጥጥር በሚያስችለው መልኩ 24 ሰዓት ክፍት አለማድረግ፣	7
3.	በተለያዩ ምክንያቶች ለአስቸኳይ ሀገራዊ ልዩ ሥራ ተሽከርካሪው በሚፈለግበት ጊዜ በሚኒስቴሩ በሚሰጠው የኮታ ድልድል መሰረት አለመፈጸም፤	20
4.	የሌላ ድርጅት ዲስክ፣ አርማና ስቲከር በተሽከርካሪዎች ላይ ለጥፎ መገኘት	15
5.	ለህገ ወጥ የሰዎች ዝዉዉር ተባባሪ መሆን እና ስደተኞችን በተሽከርካሪው ደብቆ ማጓጓዝ	10
6.	የኮንትሮባንድ እቃ ማጓጓዝ፣ ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት ወይም ወደ ጎረቤት ሀገር ይዞ መግባት፣	10
7.	ባልተመዘገቡ፣ የብቃት ማረጋገጫ ባልወሰዱና ባላደሱ ወይም በታገዱ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት መስጠት፣	10
8.	ትክክለኛ ያልሆኑና ሀሰተኛ መረጃዎችን እና ሰነዶችን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መላክ፣	20
9.	ማንኛውም ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በተሰጠበት ወቅት ተሟልተዋል በሚል ያሳያቸውን መመዘኛዎች በቁጥጥር ወቅት ተሟልተው አለመገኘት፣	10
10.	ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ባጸደቀው የስምሪት መርሀ ግብር መሰረት አለመሸፈን፣	8
11.	ባልተፈቀደ ቦታ በህገ ወጥ መንገድ በመጫን የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፣	10
12.	ለሌሎች ህገወጥ አሰራሮች መተባበር፣	20
13.	ለመስመሩ ከተፈቀደው ታሪፍ በላይ ማስከፈል ወይም/እና ትርፍ ሰው መጫን፤	15
14.	ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች (ሚዛን፣ ደንብ ልብስ፣ ባጅ እና ሌሎች) አሟልቶ አለማቅረብና ስራ ላይ አለማዋል፤	10
15.	ተሽከርካሪው በሚበላሽበት ወይም አገልግሎት መስጠት በማይችልበት ሁኔታ ሌላ ተሽከርካሪ በመተካት ተጓጉችን ማድረስ ወደ ሚገባው ቦታ አለማድረስ፤	10
16	ለዕቃ ጭነት በመመሪያው ከተቀመጠው አሰራር ውጭ ማስከፈል፤	10

2) Second category of offenses that result Administrative Measures

No	List of offence type	Weight of the offense
1.	Failing to renew the operator's qualification certificate every year according to the Directive and meeting the necessary requirements in time;	8
2.	Not keeping the system set up to monitor the company's vehicle activity open 24 hours a day in a manner that allows the ministry to control it.	7
3.	For various reasons, when the vehicle is required for urgent national special work, failure to fulfill the quota allocation given by the Ministry;	20
4.	Placing other company's disc, logo and sticker on vehicles	15
5.	Being an accomplice to human trafficking and smuggling refugees in the vehicle	10
6.	Transporting contraband, possessing illegal weapons or bringing them into a neighboring country;	10
7.	Providing services with unregistered, unqualified and no renewed or suspended vehicles;	10
8.	Sending inaccurate and false information and documents to the ministry;	20
9.	Failure of any operator to comply with the standards it demonstrated to have been met at the time of the issuance of the qualification certificate;	10
10.	Failure to cover according to the Trip schedule submitted to the Ministry and approved.	8
11.	Providing transport services by illegally loading in unauthorized places;	10
12.	Collaborating with other illegal practices;	20
13.	Charge more than the authorized tariff for the line and/or charge extra person;	15
14.	Failing to provide necessary resources for the work (balance, regulation clothes, badges and others) and not using them;	10
15.	Failing to deliver passengers to their destination by substituting another vehicle in case the vehicle breaks down or becomes unserviceable;	10
16.	Charging for cargo outside of the procedure laid down in the guidelines;	10

ሠንጠረዥ -"መ"

የኦፕሬተሩ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር መመዝገቢያ ቅጽ (በኦፕሬተሩ የሚሞላ)

የድርጅቱ ስም								
አድራሻ		ከተማ -------	ክፍለ ከተማ --------	ወረዳ ----------	የቤት ቁጥር --------	ስልክ ቁጥር ----------		
ተ.ቁ	የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ/ ቁጥር	የተሽከርካሪው ባለንብረት ስም(በኪራይ ለሚያዙ)	የሠሌዳ ቁጥር	የሞተር ቁጥር	የሻንሺ ቁጥር	የስሪት ዘመን	የወንበር ብዛት	የጎን ቁጥር
1								
2								
3								
4								
5								

ከላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች ትክክለኛ ስለመሆናቸው በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡----------

ፊርማ፡----------

ቀን፡----------

Schedule "D"

Registration form of list of the organization's vehicles /to be filled by Organization/

Name of the organization								
Adress		**City**	**sub city**	**wereda**	**house no.**	**tel.no.**		
no.	**title certificate book/** Libre / number	**vehicles owner name/rent/**	**Plate no.**	**engine no.**	**Chassis Number**	**year of make**	**number of seat**	**side no.**

I certify the above information are correct by signature

Full name: _____

Signature: _____

Date: _____